# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 039 ጥቅምት 9 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




አምባሳደር ዲና ሙፍቲ



አባ ገዳ ጎበና ሆላ



ኡስታዝ አቡበከር አህመድ

# የወል እሴቶቻችንን

## ለሰላም ግንባታ እንዴት እንጠቀምባቸው?

**አዲሱ ገረመው**

ታላቅን ማክበር፣ መደማመጥ፣ ለአባቶች ቦታ መስጠት፣ እርቅ መፈጸም፣ መታዘዝ፣ መረዳዳትና መሰል የሥነ ምግባር መርሆዎች የኢትዮጵያዊያን የጋራ እሴቶች መሆናቸው ይነሳል። እነዚህን የወል እሴቶች በመጠቀም ችግሮችን ፈትቶና አስታርቆ፤ የተበላሸን አቅንቶ፤ የነገውን መልካም ተስፋ አሳይቶ በይቅርታና በፍቅር መኖር እንደሚቻል ምሁራን፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት መምህራን ይናገራሉ።

የእስልምና ሃይማኖት መምህሩ ኡስታዝ አቡበከር አህመድ እንደሚናገሩት፤ የእምነት መለያና መልካም እሴቶች አላቸው ከሚባሉት ሀገራት ውስጥ ኢትዮጵያ ትልቁን ድርሻ ትይዛች። እንደ ሀገር ትልልቅ ችግሮች በሽምግልናና በንግግር እንደተፈቱ የሀገሪቱ የረጅም ጊዜ ታሪኮች ያሳያሉ። በአባቶች ጥረት በይቅርታ የታለፉ ብዙ ጉዳዮችም አሉ። ችግሮች ሲፈጠሩ መወያየትና መነጋገር እንደሚቻል ታላላቆች አቅጣጫዎችን አሳይተዋል። እንዲህ አይነት ሚና ያላቸው አባቶች፣ ታላላቆችና የሃይማኖት አባቶች ዛሬም አሉ።

ችግሮች ሲፈጠሩ የሀገር ሽማግሌዎች፣ አባቶችና እናቶች ጉዳዮቹን በቤተሰብ ደረጃ ለመፍታት የሚይዙበት መንገድ እንዳለ የሚናገሩት ኡስታዝ አቡበከር፤ የሰው ህይወት የጠፋባቸው ትልልቅ ችግሮች ሳይቀሩ በተለያየ ባህልና ማንነት ቁጭ ብሎ ማየትና መፍታት የሚችል እሴት በሀገር ደረጃ መኖሩን ይገልጻሉ።

“ከሥነ ምግባር ጋር ተያይዞ መገለጫ የሆኑ፤ እንደ ኢትዮጵያ የምንታወቅባቸው በርካታ የጋራ እሴቶች አሉን። የተለያየ ባህልና ሃይማኖት ማንነት ያለን ሕዝቦች ነን። በዚህ ማንነት ውስጥ መከባበር፣ መተሳሰብ፤መረዳዳት፤ አንዱ ስለአንዱ ችግር መኖር፤ አንዱ ለአንዱ እውቅና የመስጠትና ተያያዥ የጋራ የሆኑ እሴቶቻችን እንደ ማህበረሰብ ኢትዮጵያዊነታችንን የሚገልጹ ናቸው። በመረዳዳታችን ከራሳችን አልፈን ለሌላው ማህበረሰብ በምንሰጠው ክብርና ቦታ የምንታወቅበት እሴትና

**የወል እሴቶቻችንን... ወደ ገጽ4 ዞሯል**
















## መንግሥት የፋይናንስ አካታችነትን እውን በማድረግ ስኬት አስመዝግቧል

### - የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት አስጀመረ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት የባንክና የኢንሹራንስ ኢንዱስትሪ አዋጆችን በመከለስና በማሻሻል የፋይናንስ አካታችነትን እውን ለማድረግ የተከተለው መንገድ ስኬት እንዲመዘገብበት ያስቻለ መሆኑን የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ‹‹ዲቢኢ ተዐውን›› ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት አስጀመረ፡፡

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ እዩብ ተካልኝ (ዶ/ር)፤ በማስጀመሪያ መርሀ ግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ የፋይናንስ ተደራሽነትና አካታችነትን እውን ለማድረግ በመንግሥት የተለያዩ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡

በተለይም የባንክና የኢንሹራንስ ኢንዱስትሪ አዋጆችን በመከለስና በማሻሻል የፋይናንስ አካታችነትን እውን ለማድረግ የተከተለው መንገድ ስኬት ተመዝግቧል፡፡

**መንግሥት የፋይናንስ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**



## ‹‹የባህር በር ለአንድ ሀገር ሁለተናዊ ሉዓላዊነት መረጋገጥ ወሳኝ ሚና አለው››

አየለ በከሪ(ዶ/ር)

- የታሪክ ተመራማሪ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገትና ሉዓላዊነት መረጋገጥ የባህር በር ጉልህ ሚና እንደሚጫወት የታሪክ ተመራማሪው ተ/ፕሮፌሰር አየለ በከሪ(ዶ/ር) ገለጹ።

ተ/ፕሮፌሰር አየለ በከሪ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገትና ሉዓላዊነት መረጋገጥ የባህር በር ጉልህ ሚና አለው። ከዚህ መነሻነት ኢትዮጵያ አስፈላጊውን ሰላማዊ ንግግሮች በማድረግና

**‹‹የባህር በር... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## “በጎታች ነገሮች ከዓላማችን ሳንዘናጋ ከሠራን ሀገር ከፈተና እንድትወጣ የራሳችንን አሻራ እናሳርፋለን”

-ፕሮፌሰር አፈወርቅ ካሡ

የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በዙሪያችን የሚፈጠሩ ጎታች ነገሮች ከዋናው ዓላማችን እንዳያስቱን ተሰናስለን ከሠራን ሀገር ከፈተና እንድትወጣ የራሳችንን አሻራ ማሳረፍ እንችላለን ሲሉ የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር አፈወርቅ ካሡ ገለጹ፡፡

**“በጎታች ነገሮች... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**












ኤርጎጊ ተስፋዬ (ዶ/ር)

# ዓለም አቀፍ ሥርዓትን መሰረት ያደረገ የሕፃናት ድጋፍና ክብካቤ መመሪያ ክለሳ ተደረገ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ዓለም አቀፍ ሥርዓትን ያቀፈና ሕጻናት አማራጮች እንዲኖራቸው የሚያደርግ ድጋፍና ክብካቤ መመሪያ ላይ ክለሳ መደረጉን ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር አስታወቀ።

በመርሀ ግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ መንግሥት በተለይ ወላጆቻቸውን ላጡና ለችግር ለተጋለጡ ሕጻናት ጥበቃና ክብካቤ በማድረግ ጤናማ የኅብረተሰብ ክፍል ሆነው እንዲያድጉና ለሀገራቸው መልካም ዜጋ እንዲሆኑ በማሰብ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም የችግሩን አሳሳቢነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በ2009 ዓ.ም የተለያዩ የድጋፍና ክብካቤ አማራጮችን የያዘ መመሪያ በመንደፍ ሥራ ላይ እንዲውል አድርጎ ነበር።

ነገር ግን ይህ ሥራ ላይ የዋለው መመሪያ ጥልቀት የሌለውና የበለጠ አማራጮችን እያካተተ የሚሄድ ባለመሆኑ በጥናት በተደገፈ መልኩ ክለሳ እንዲደረግለት ተደርጓል። በዚህም መመሪያው የተሻለ አማራጭ፣ ድጋፍና ክብካቤ እንዲያስተዋውቅ እንዲሁም ሕጻናትን የሚያግዙ ፕሮግራሞችን በተሳካ ሁኔታ እንዲተዋወቁ የሚያደርግ ነው ብለዋል።

የተከለሰው መመሪያ መንግሥት ያመነበት፣ የዓለም አቀፍ ሥርዓት ያቀፈና ሕጻናት የተለያዩ አማራጮች እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው ብለዋል ሚኒስትሯ።

የነገ ተስፋ የሆኑ ሕጻናት በመልካም ጤንነትና ስብዕና ታግዘው እንዲያድጉ፣ እድገታቸውን ሊያሰናክሉ ከሚችሉ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመጠበቅ አስፈላጊው ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል ብለዋል፤ በተለይም በተለያዩ ሰው ሰራሽ መንስኤዎች ሳቢያ ለከፋ ችግር የተጋለጡ ሕጻናት የሚገባቸውን ትኩረት አግኝተው እንዲያድጉና የወደፊት ህይወታቸው የተቃና እንዲሆን ሁሉም ኃላፊነት አለበት ብለዋል።

ዶ/ር ኤርጎጌ፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሀገር ውስጥ ጉዲፈቻን እንደተጨማሪ ክብካቤ ፕሮግራም በመውሰድ በተለያዩ ምክንያቶች ከቤተሰቦቻቸውና ከአካባቢያቸው የራቁ ሕጻናትን ወደ ቤተሰቦቻቸውና ወደ ማኅበረሰቡ እንዲቀላቀሉ የማድረግ ሥራዎች ሲሠራ ቆይቷል ሲሉ ገልጸው፤ በዚህም በርካታ ሕጻናትን መደገፍና ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

ሆኖም ከመንግሥት ጥረት ጎን ለጎን ኅብረተሰቡና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሕጻናቱን ህይወት ለማሻሻልና ወደፊት ተስፋቸውን ለማለምለም እያገዙ በመሆኑ ይህን አጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ብለዋል።

ለመመሪያው ዝግጅት ትብብር ያደረጉ ዩ.ኤስ. ኤይድ፣ ቤታኒ ክርስቲያን እና ሌሎችም አካላትን በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስም ተመስግነዋል፤ ላበረከቱት አስተዋጽኦ እውቅና ተሰጥቷል።

# በሙስናና ብልሹ አሠራር የተጠረጠሩ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት አመራሮችና ሠራተኞች በቁጥጥር ስር ዋሉ

አዲስ አበባ፡- በሙስናና ብልሹ አሠራር የተጠረጠሩ 42 የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት አመራሮችና ሠራተኞች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የጋራ ግብረ-ኃይሉ አስታወቀ።

ከኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት አሠጣጥ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት ከብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት፣ ከኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ፣ ከኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አስተዳደርና ከኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት የተውጣጣ ግብረ-ኃይል ምርመራ ሲያደርግ ቆይቷል።

የጋራ ግብረ-ኃይሉ እንዳስታወቀው፤በሙስናና ብልሹ አሠራር የተጠረጠሩ 42 የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት አመራሮችና ሠራተኞች በቁጥጥር ስር ውለዋል።

ተገልጋዮች ፓስፖርትና መሰል አገልግሎቶችን በአፋጣኝና በአነስተኛ ዋጋ ማግኘት እንደሚችሉ የገለጸው መግለጫው፤ ተጠርጣሪዎች የፈጠሯቸው የተወሳሰቡ አሠራሮች ዜጎችን ለከፋ እንግልትና ላልተገባ ወጪ ሲዳርጉ እንደነበር ገልጿል።

ተጠርጣሪዎቹ ከፍተኛ ገንዘብ በመጠየቅ በሙስና ተግባር መሰመራታቸውና የግል ጥቅማቸውን ሲያሳድዱ እንደነበር በመግለጽ፤ ዜግነት ለሌላቸው የውጭ ሀገራት ዜጎች፣ በወንጀል ተከሰው የጉዞ ሰነዳቸው ለታገደባቸው፣ ሐሰተኛ የማንነት መገለጫ ላላቸው፣የፓስፖርት፣ ሊሴፓሴና ቪዛ አየር በአየር በመሸጥ ፣ ማስተላለፍን ጨምሮ መንገደኞች በሌሉበት ጉዞ እንዳላቸው በማስመሰልና ወደ ተለያዩ ሀገራት እንደተዘዋወሩ የሚገልፅ ማሕተም በማዘጋጀት ተግባር ተሰማርተዋል ብሏል።

ከሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ተመልምለው ያለፉ እንደሆኑ በማስመሰል ግለሰቦች ባልተገባ መንገድ ለሥራ ወደ ተለያዩ የዓረብ ሀገራት እንዲወጡ ማድረጋቸውን ጠቅሶ፣ የሕጋዊ ግለሰብን ፓስፖርት ፎቶግራፍ በመቀየር ከፍተኛ የማጭበርበር ወንጀል ሲፈጽሙ እንደተደረሰባቸው የግብረ-ኃይሉ መግለጫ ጠቁሟል።

ወንጀለኞች ከአዲስ አበባ እስከ ክልሎች የጥቅም ትስስር በመዘርጋት ሙስና ሲፈጽሙ ከመቆየታቸውም ባሻገር፤ ሐሰተኛ የማንነት መታወቂያዎችን በማዘጋጀት ተግባር ላይ ተሰማርተው ከነበሩ የውጭ ሀገር ዜጎች ጋርም ግንኙነት በመፍጠር ወንጀሉን ሲፈፅሙ እንደቆዩም ገልጿል።




የጋራ ግብረ-ኃይሉ ባደረገው ክትትል ከ200 በላይ የሚሆኑ በሕገወጥ መንገድ የተዘጋጁ ፓስፖርቶች እንዲመከኑ መደረጉን በመጥቀስ፤ የወንጀል ድርጊቱም መንግሥትን በሚሊዮን የሚቆጠር የውጭ ምንዛሪ እንዳሳጣው ተመላክቷል።

ምርመራው በአዲስ አበባ ከተማ፤ ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ሲዳማ፣ ሶማሌ፣ ጋምቤላና ቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልሎች መደረጉን የገለጸው ግብረ -ኃይሉ፤ በወንጀሉ የተሳተፉ በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ሲያገለግሉ የነበሩ 42 ተጠርጣሪዎች በሕግ ቁጥጥር ስር መዋላቸውን ገልጿል።

በሕግ ቁጥጥር ስር ከዋሉ ተጠርጣሪዎች መካከልም የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር የነበሩት ታምሩ ግንበቶን ጨምሮ ሌሎችም እንደሚገኙበት ግብረ-ኃይል አስታውቋል።

ተጠርጣሪዎች ዙሪያ የሚደረገው ምርመራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል በመግለጽም፤ በግለሰቦቹ ዙሪያ ተጨማሪ መረጃ ያላቸው ዜጎች ለፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ጥቆማ መስጠት እንደሚችሉም ገልጿል።

በኦፕሬሽኑ በተደረገ ብርበራ የተለያዩ ፓስፖርቶች፣የሀገራት የብር ኖቶች፣ ሐሰተኛ መታወቂያዎች፣ አየር በአየር የወጡ ሊሴ ፓሴዎችና የታተሙ ቪዛ ካርዶች በተጠርጣሪዎቹ መኖሪያ ቤትና የሥራ ቦታ በኢግዝቢትነት መያዛቸወን ግብረ -ኃይሉ አመልክቷል።

ግብረ -ኃይል መሰል ሕገ ወጥ ተግባራት ዙሪያ የሚያካሂደውን ምርመራ፣ ክትትልና ኦፕሬሽን አጠናክሮ እንደሚቀጥል በመግለጽ፤ ለኦፕሬሽኑ መሳካት ማኅበረሰቡ ላሳየው የተለመደና ቀና ትብብር ምስጋናውን አቅርቧል።

# የደብተር ስርጭት በመዘግየቱ ተቸግረናል

– ተማሪዎች

# በቀጣይ ሁለት ሳምንታት ደብተር ሙሉ በሙሉ ይሰራጫል

–የአዲስ አበባ ምገባ ኤጀንሲ

**ማህሌት ብዙነህ እና ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 የትምህርት ዘመን የደብተር ስርጭት በመዘግየቱ መቸገራቸውንና ወላጆቻቸው ለተጨማሪ ወጪ መዳረጋቸውን የአዲስ አበባ ከተማ የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ገለጹ። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ ኤጀንሲ በበኩሉ በቀጣይ ሁለት ሳምንታት የተማሪዎች ደብተር ሙሉ በሙሉ ይሰራጫል ሲል አስታውቋል።

የ11ኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው አዝመራ ይርጋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸችው፤ ደብተር የተሰጠው ትምህርት ከተጀመረ ቆይቶ ነው። እሱም ቢሆን የተሟላ አይደለም።

ተማሪዎች መንግሥት ደብተር ያቀርባል በሚል ተስፋ ደብተር ሳይገዙ ሲጠባበቁ ነበር። አንዳንድ ተማሪዎችም በአምናው ደብተራቸው እንዲሁም በአንድ ደብተር ላይ ሁሉንም ትምህርት ሲማሩ ቆይተዋል። አብዛኛው ተማሪም ደብተር ከተሰጣቸው በኋላ የተማሩትን ትምህርት በመገልበጥ ላይ ይገኛሉ ብላላች።

የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ የሆነውና ስሙን መግለጽ ያልፈለገው ተማሪ በበኩሉ፤ ትምህርት የተጀመረው ደብተርም ሆነ ዩኒፎርም ሳይሟላ መሆኑን በመጥቀስ፤ እኔ አምና በተሰጠኝ አምስት ደብተር ስማር ብቆይም ብዙ ተማሪዎች ግን በአንድ ደብተር ብዙ የትምህርት አይነቶችን እየተማሩ ነው ያሳለፉት ሲል ገልጿል።

መምህራን ደብተር ይዘን ባለመገኘታችን እና የሚሰጡትን ማስታወሻዎች ባለመያዛችን አይረዱንም ያለው ተማሪ፤ የካሌብ ወላጆችም ይህን ሲያዩ ደብተር በግል ለመግዛት ተገደዋል ብሏል። “አሁን ላይ ደብተር ተሰጥቶናል፤ ስለዚህ ለቀጣይ አመት ያገለግለናል ብለን ስላሰብን ወስደናል” ሲልም አክሏል።



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ ኢጀንሲ ምክትል ዳይሬክተር እና የግብዓት አቅርቦት ኃላፊ አቶ ሚነወር ኑረዲን ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ለሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የደብተር አቅርቦት በቀጣይ ሁለት ሳምንታት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ተደራሽ ይደረጋል።

በተያዘው የትምህርት ዘመን ከስምንት ሚሊዮን በላይ ደብተር ያስፈልጋል ያሉት አቶ ሚነወር፤ ይህም ከ997 ሺህ 461 በላይ ለሆኑ ተማሪዎች ተደራሽ የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል።

በመሆኑም መስከረም 22 ቀን 2016 ዓ.ም ደብተሮቹን ከውጭ ሀገራት በማስገባት የመጀመሪያ ዙር የደብተር ስርጭት የተደረገ ሲሆን ከ3 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ደብተር በከተማው ክፍለ ከተሞች ለሚገኙ ትምህርት ጽህፈት ቤቶች ስርጭት ተደርጓል። ቀጣይ ዙር በሁለት ሳምንታት ውስጥ አጠቃላይ ስርጭት ይከናወናል ሲሉም ገልጸዋል።

ኤጀንሲው ከቅድመ አንደኛ እስከ 12ኛ ክፍል ላሉ ከ997 ሺህ 461 በላይ የመንግሥት ተማሪዎች የትምህርት ግብዓት ቁሳቁስ እና የደንብ ልብስ አቅርቦት እንዲሁም ከ79 ሺህ በላይ መምህራን እና ከ16 ሺህ በላይ ለሚሆኑ መጋቢ እናቶች ጭምር የጋውንና የደንብ ልብስ ያቀርባል ሲሉ ገልጸው ፤ ለዚህም ከተማ አስተዳደሩ ሙሉ ወጪውን እንደሚሸፍን አቶ ሚነወር አስታውቀዋል።

ደብተሮችን እና የደንብ ልብሶችን በትምህርት መጀመሪያ ሳምንታት ውስጥ ወደ ስርጭት ለማስገባት ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በተለያዩ የአቅራቢዎች አቅምና ጥራት ማነስ እንዲሁም ምርቶቹ ከውጭ የሚገቡ በመሆኑ በመጓጓዣ ትራንስፖርት ተግዳሮት ምክንያት ሊዘገይ የቻለ መሆኑን አስታውቀዋል።

በሌላም በኩል በሀገር ውስጥ ያሉ አቅራቢዎች ጥራት ያላቸውን ምርቶችን በማቅረብ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጠይቀዋል፡

የጥቁር አንበሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር የሆኑት አቶ ገዙ በለጠ እና የአዲስ ከተማ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ እንዳልካቸው ደጀኔ በበኩላቸው፤ ትምህርት ቤቶቹ ደብተሮችን ከማዕከል በመረከብ ለእያንዳንዱ ተማሪ ስድስት ስድስት ደብተር እንዲዳረስ መደረጉን ጠቁመው፤ በቀጣይ ከኤጀንሲው ደብተር ሲቀርብ የቀረውን እንደሚያከፋፍሉ ተናግረዋል።

ለተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የመማሪያ ደብተር እና ግብአት ማሟላት ለትምህርት ጥራት ብሎም ብቁ ዜጋ ማፍራት ላይ ትልቅ ሚና አለው ያሉት ርዕሰ መምህራኑ፤ ይህንንም በመረዳት መንግሥት አስፈላጊውን ትኩረት መስጠት አለበት ሲሉ ገልጸዋል።

# ሃሰተኛ ዘገባና የጥላቻ ንግግር በሚያሰራጩ ግለሰቦችና የሚዲያ ተቋማት ላይ ማስተካከያ መወሰድ እንዳለበት ተገለጸ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ከሙያዊ ሥነ-ምግባር ባፈነገጠ መልኩ የሃሰት ዘገባና የጥላቻ ንግግርና በማሰራጨት ማኅበረሰቡን የሚያደናግሩ ግለሰቦችና የሚዲያ ተቋማት ላይ ማስተካከያ መወሰድ እንዳለበት ተገለጸ።

ሚዲያው የሚጠበቅበትን ኃላፊነት መወጣት በሚችልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ የምክክር መድረክ ትናንት ተካሂዷል።

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ምክር ቤት ሰብሳቢ አቶ አማረ አረጋዊ በምክክር መድረኩ ላይ እንደተናገሩት፤ በሃሰት ዘገባና በጥላቻ ንግግር ምክንያት የማኅበረሰቡ አንድነትና ሰላም እየተሸረሸረ ነው። ይህንንና መሰል ተግባራት የሚያደርጉ አካላትን ሁሉም በጋራ መዋጋት አለበት።ሥራቸውን በአግባቡ የሚሰሩ ሚዲያዎችና ግለሰቦች እንዳሉ ሁሉ ከሙያዊ ሥነ-ምግባር ባፈነገጠ መልኩ የሃሰት ዘገባና የጥላቻ ንግግር በመንዛት ችግር የሚፈጥሩ አሉ ያሉት አቶ አማረ፤ መንግሥትና የሚመለከታቸው አካላት ማስተካከያ መውሰድ አለባቸው ብለዋል።


አቶ አማረ አረጋዊ


አቶ አደራው ገነቱ

አቶ አማረ አክለውም፤ የኢትዮጵያ ሚዲያ ሴክተር አልያንስ (EMSA) የሚዲያውን እንቅስቃሴ ለማሳለጥ የተቋቋመ መሆኑን ጠቅሰው፤ በኢትዮጵያ የፕሬስ ነጻነት ለማምጣት፣ ሙያዊ ድጋፍ ለማድረግ እንዲሁም በዘርፉ ችግሮች ሲያጋጥሙ በቀላሉ ማስወገድ ላይ እንደሚሰራ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አማረ ገለጻ፤ የጥላቻ ንግግርና የሃሰት ዘገባ በአንድነትና በሰላም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ በመሆኑ ትኩረት ተደርጎ መሰራት አለበት።

በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት የባህልና የሳይንስ ድርጅት (UNESO) የኢትዮጵያ ተወካይና የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኃላፊ አቶ አደራው ገነቱ በበኩላቸው፤ የሃሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግር ለመቋቋም ጠንካራ የሆነ የመረጃ ፍሰት እንዲሁም የሚዲያ ንቃተ ህሊና ማሳደግ ያስፈልጋል ብለዋል።

እንደ አቶ አደራው ገለጻ፤ የሚዲያ ንቃተ ህሊና እንዲመጣና የጥላቻ ንግግር እንዲቀር ማኅበረሰቡ፣ መንግሥት እንዲሁም የሚዲያ ተዋንያን በትብብር ሊሠራ ይገባል።

ኅብረተሰቡም መረጃ በማጣራት ረገድ ግንዛቤ መውሰድ አለበት ያሉት አቶ አደራው፤ ኢትዮጵያ ላይ ያለውን የሚዲያ እንቅስቃሴ ለማሳደግ በአንድ ተቋም አልያም በተወሰኑ አካላት ሥራ ሳይሆን የሁሉም ርብርብ ያስፈልጋል ብለዋል።

በምክክር መድረኩ የሚዲያ ባለሙያዎች፣ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ሚዲያ ሴክተር አልያንስ(EMSA)፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ድርጅት ኅብረት፣ የUNESCO ተወካዮች እንዲሁም ዓለም አቀፍ የሚዲያ ድጋፍ(IMS)ተገኝተዋል።

# በክልሉ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት 23 ሺህ 500 ሔክታር በዘር ይሸፈናል

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- በ2016 ዓ.ም በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት 23 ሺህ 500 ሄክታር መሬት በዘር እንደሚሸፈን የአፋር ክልል የእንስሳት፣ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ።

በቢሮው የሰብል ልማት ዳይሬክተር አቶ አሕመድ መሐመድ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በአፋር ክልል አጠቃላይ በምርት ዘመኑ 100 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በዘር ለመሸፈን ታቅዶ በስፋት እየተሰራ ይገኛል። ከዚህም ውስጥ በመስኖ ስንዴ 23 ሺህ 500 ሄክታር መሬት በዘር ለመሸፈን ታቅዷል።

የአዋሽ ወንዝ ተፋሰስን ተከትሎ በዞን አንድና ዞን ሦስት ስር በሚገኙ ወረዳዎች ላይ የመስኖ ስንዴ ላይ ትኩረት በማድረግ አርብቶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮችና ማህበራት የመሬት ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛሉ ብለዋል።

በበጋ መስኖ ስንዴ ከሚለማው መሬት ከ21 ሺህ ሄክታሩ በላይ የሚሆነው በባለሀብቶች፣ የተቀረው ደግሞ በከፊል አርብቶ አደሮችና በማኅበራት የሚለማ መሆኑን አቶ አህመድ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አህመድ ገለጻ፤ ባለፈው ዓመት በተከናወነው ሥራ የነበሩ ተግዳሮቶችንና ምቹ አጋጣሚዎችን በመለየት ወቅቱን በጠበቀ መልኩ የበጋ ስንዴ እርሻ ቀደም ብሎ ከሚከናወንባቸው ዞኖች በተጨማሪ ዞን አምስት ላይ የሚገኙ አዲስ አካባቢዎች ላይ ምርቱ ይለማል።

በግብርና ስራው ሜካናይዜሽንን በስፋት በመጠቀም ወደሥራ እንደሚገባ አመላክተው፤ በክልሉ በተቋቋመው የቴክኒክ ቡድን አማካኝነት በፕሮጀክቶችም ሆነ በሌሎች ድጋፎች የመጡ የእርሻ ትራክተሮች ያሉበትን ሁኔታ በማረጋገጥ ወደሥራ ለመግባት ዝግጅቶች እየተደረጉ እንደሆነ አስታውቀዋል።

ከመስኖ ስንዴ ልማት ባለፈ በመኸር እርሻ ሥራ 30 ሺህ ሄክታር ለማልማት ታቅዶ ከ22 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በዘር መሸፈን ተችሏል ብለዋል።

በክልሉ ዞን አንድና በዞን ሦስት በሚገኙ ወረዳዎች ማሽላ፣ ስንዴ፣ በቆሎ እና የመሳሰሉ ሰብሎችን ማልማት መቻሉን ዳይሬክተሩ አንስተዋል።

በተጨማሪም ማሾ፣ ሰሊጥ፣ በሎቄ፣ ጥጥ፣ ሽንብራ፣ ጤፍና ገብስ በስፋት ለማልማት እቅድ ተይዟል ሲሉ አመላክተዋል።

በመኸር እርሻው የምርት አሰባሰብ ወቅት የምርት መባከን እንዳይፈጠር የቢሮው አመራሮችም ጭምር ያሉበት የቴክኒክ ቡድን ሙያዊ ድጋፍና የክትትል ሥራ በማከናወን ከአስተራረስ ጀምሮ እስከ ምርት አሰባሰብ ድረስ በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን ጥረት እያደረገ ነው ብለዋል።

ባለፈው የምርት ዘመን ከክልሉ አቅም በላይ የሆኑ ተግዳሮቶች እንደነበሩ አንስተው፤ በተለይ የግሪሳ ወፍ በስንዴ ምርት ላይ ትልቅ ተግዳሮት እንደነበር አስታውሰዋል።

በቀጣይም የግብርና ግብዓቶችን በማቅረብና በሰብል ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ተባዮችን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት የሚመለከታቸው የፌዴራል ተቋምት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

# በአማራ ክልል ከ37 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የበቆሎ ምርት ሊሰበሰብ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በመኸር ወቅት ከታረሰው 643 ሺህ ሄክታር መሬት ከ37 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የበቆሎ ምርት ሊሰበሰብ መሆኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

በአማራ ክልል ግብርና ቢሮ የሰብል ልማትና ጥበቃ ዳይሬክተር አቶ አግደው ሞላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ክልሉ በመኸር ወቅት 592 ሺህ ሄክታር መሬት በበቆሎ ዘር ለመሸፈን አቅዶ ከ643 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በበቆሎ ዘር መሸፈን ችሏል። ከዚህም ከ37 ሚሊዮን ኩንታል በላይ በቆሎ ይሰበሰባል።

ይህም ክልሉ በበቆሎ ምርት ከፍተኛ የሆነ አቅም እንዳለው ያሳያል ያሉት አቶ አግደው፤ ዘንድሮ ዝናብ ቀደም ብሎ በመዝነቡ ለአገዳ ሰብሎች ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል። ይህም ለእርሻና ለዘር ሽፋን እንቅስቃሴና ለምርታማነት በጎ እድል ፈጥሯል ብለዋል።

አምና አርሶ አደሮችና ባለሀብቶች ለበቆሎ ምርት ከፍተኛ ፍላጎት በማሳየታቸው ክልሉ የዘንድሮውን የበቆሎ ዘር ሽፋን አሳድጓል ያሉት አቶ አግደው፤ ክልሉ 27 ከሚደርሱ የዘር አባዢ ድርጅቶች ጋር በመተባበር አዳዲስ የበቆሎ ዝርያዎችን ለአርሶ አደሩ ያቀርባል ሲሉ ገልጸዋል።

ከድርጅቶቹ በቀጥታ የገበያ ሥርዓት ለአርሶ አደሩ ምርጥ ዘር ሲቀርብ መቆየቱን የተናገሩት ኃላፊው፤ ይህም ህገወጥ ደላሎችን እና አላስፈላጊ ድካምን በመቀነስ ምርታማነት ላይ የበኩሉን ሚና ይጫወታል ብለዋል።


አቶ አግደው ሞላ

በክልሉ 27 ሺህ ኩንታል የሚደርስ የበቆሎ ምርጥ ዘር በክልሉ እየተባዛ ለአርሶ አደሩ እንዲቀርብ ይደረጋል ያሉት አቶ አግደው፤ በዚህ የአርሶ አደሩን እና የባለሀብቱን ፍላጎት ሙሉ ለሙሉ ማሟላት ባይቻልም ተደራሽ ማድረግ ግን ተችሏል። ከተሠራጨው ምርጥ ዘርም በሄክታር 55 ኩንታል በቆሎ ማግኘት እንደሚቻል ገልጸዋል።

አርሶ አደሩ በቆሎ ለማምረት ያለው ፍላጎት፣ አርሶ አደሩ ዘር እንዲያባዛ መደረጉ፣ ክልሉ የግል እርሻዎችን በመጠቀም የኮንትራት የዘር አመራረት ሂደትን በመከተሉ እና ከፌዴራል መንግሥት የሚመጡ ምርጥ ዘሮችን በመቀበል ተግባራዊ ማድረግ በክልሉ ከተሰሩ ሥራዎች ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው ነው ያሉት አቶ አግደው።

በውጭ ሀገር ተቋማት የሚመረት ዘር ማነስ፣ የማዳበሪያ እጥረት እና የክልሉ ሰላምና ጸጥታ በዘንድሮ ዓመት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች መሆናቸውንም ገልጸዋል።



እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)



ዮሐንስ አያሌው (ዶ/ር)



ሼህ አብዱልከሪም በድረዲን

# መንግሥት የፋይናንስ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት ራሱን ችሎ እንዲደራጅ ሕጋዊ ማእቀፍ ኖሮት እንዲተገበር መደረጉን ጠቅሰው፤ የፋይናንስ አካታችነትን እውን ለማድረግ እየተሰሩ ካሉ ሥራዎች ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት አንዱ መሆኑን ነው የጠቆሙት።

ከሸሪዐ መሪዎች ጋር በመተባበር የሚሰጥ መሆኑን በመጠቆምም፤ አገልግሎቱ ቴክኖሎጂ ተጨምሮበት ሲቀርብ ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት እጅግ የጎላ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት አመልክተዋል።

ባንኩ ከከፍተኛ ችግር ወጥቶ የስኬት ምልክት መሆን የቻለው መንግሥት በወሰደው ጠንካራ ርምጃ መሆኑን ተናግረዋል።

ሰፊውን ሕዝብ ለመጥቀም የባንኩን ውጤታማነት ለማረጋገጥ መሰራት እንዳለበትም ሚኒስትር ደኤታው አሳስበዋል። መርሀ ግብሩን ማስጀመር ብቻ ሳይሆን መከታተልና መደገፍ ያስፈልጋል። መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል።

የባንኩ የቦርድ ሰብሳቢ ተገኘወርቅ ጌቱ (ዶ/ር)፤ ባንኩ ተጋርጦበት ከነበረው የህልውና አደጋ መንግሥት በወሰደው ርምጃ ከኪሳራ ወጥቶ ውጤታማና አትራፊ ከሆኑ ተቋማት ተርታ መሰለፍ መቻሉን ጠቁመዋል።

ለባንኩ ሁለንተናዊ ስኬት የቦርድ አመራሩ ድጋፍ አይለየውም ብለዋል። ባንኩ አገልግሎቱን ያስጀመረው ሰፊ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች መኖራቸውን በማመን ነው፤ በርካቶችን ወደ ኢንቨስትመንት የመሳብ እምቅ አቅም ያለው በመሆኑ የፋይናንስ ተደራሽነትና ፍትሐዊነትን በማስጠበቅ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ነው ተገኘወርቅ (ዶ/ር)ያሉት።

የባንኩ ፕሬዚዳንት ዮሐንስ አያሌው ዶ/ር በበኩላቸው፤ ህብረተሰቡ እንደፍላጎቱና እምነቱ አገልግሎት ሳያገኝ ቆይቷል። ለውጡን ተከትሎም እየተስፋፋ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት በሚፈለገው መጠን ሳያድግ መቆየቱን ተናግረዋል። ነገር ግን ለውጡን ተከትሎ መንግሥት በሰጠው ትኩረት አበረታች ውጤቶች እየተመዘገቡ ናቸው። ከ18 ባንኮች በተገኘው መረጃ መሰረት 200 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ተቀማጭ ገንዘብ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ማሰባሰብ ተችሏል ሲሉ እንደአብነት ጠቅሰዋል።

የተጀመረው ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት በግብርናው፣ በአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ በአምራች ኢንዱስትሪ፣ በማእድን ልማት፣ በኮንስትራክሽን ግብአቶችና በአስጎብኚ ዘርፍ ለሚሰማሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የባንክ አገልግሎት ለማቅረብ እንደሚያስችልም አመልክተዋል።

የተጀመረው ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት ዋናውን መስሪያ ቤትን ጨምሮ በሁሉም የባንኩ ቅርንጫፎች እንደሚሰጥ ለማድረግ የአሰራር መዋቅር መዘርጋቱን ተናግረዋል።

የሸሪዐ እውቀት ያላቸው አማካሪዎች ከባንኩ ጋር በመተባበር የምክር አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ።

በመንግሥት በተወሰደው ርምጃ ባንኩ የተበላሸ ብድርን ከ40 በመቶ በላይ የነበረው ወደ ሰባት በመቶ ዝቅ እንዲል፣ ከኪሳራ ወጥቶ እአአ በ2018 ከታክስ በፊት ስድስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር እንዲያተርፍ መደረጉን አስታውሰዋል።

የመንግሥት ድጎማን ጨምሮ የባንኩ ካፒታሉ ከሁለት ቢሊዮን ብር በመነሳት በ2015 ዓ.ም 38 ቢሊዮን ብር እንዲደርስና የባንኩ ጠቅላላ ሀብት ከ80 ወደ 160 ቢሊዮን ብር እንዲያድግ እንደተቻለም ጠቁመዋል። አገልግሎቱን ቀልጣፋ፣ ግልጽና ፍትሃዊ ከማድረግ አኳያ የባንኩ ቅርንጫፎችም ከ77 ወደ 100 እንዲያድግ ተደርጓል።

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት ሼህ አብዱል ከሪም በድረዲን፣ አገልግሎቱ በመጀመሩ አመስግነው፤ ከሃይማኖት ከብሄር ምንም አይነት አጀንዳ የሌለው ልማታዊ ባንክ መሆኑን ተናግረዋል። ሙስሊሙ ኅብረተሰብ ከባንኩ ተጠቃሚ እንዳይሆን ተደርጎ እንደነበርም አስታውሰዋል።

የእሰልምና እምነት ተከታዮች የባንኩን ሕግና ደንብ በማክበር ከወለድ ነጻ ብድርን በመጠቀም በሀገር ልማት እንዲሳተፉ አደራ ብለዋል። ሕዝቡ በተመቻቸው ዕድል በመጠቀም ከመንግሥት ጎን መሰለፍ ይኖርበታል፤ ከድህነት ለመውጣት የሚደረገውን ትግል ሊያግዝ ይገባል ብለዋል።

# ‹‹የባህር በር...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የጎረቤት ሀገራትን በማሳመን የባህር በር እንዲኖራት ማድረግ የምትችልበት ዕድል አለ።

ኢትዮጵያ በአክሱም ዘመነ መንግሥት ሰፊ ግዛት ስለነበራት አዱሊስ የሚባል ጥንታዊ የባህር በር እንደነበራት አስታውሰው፤ ይህን ወደብ በመጠቀምም እስያ፣ ሰሜን አፍሪካና የገልፍ ሀገራት ድረስ የተስፋፋ የንግድ እንቅስቃሴ ታደርግ ነበር። ለዚህም በተለያዩ ሀገራት በአርኪኦሎጂስቶች የተገኙ የኢትዮጵያ ገንዘቦች ማረጋገጫ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የአክሱም ስልጣኔ በዓለም ላይ ካሉ አራት ታላላቅ ስልጣኔዎች አንዱ ተደርጎ እንደሚወሰድ አስታውሰው፤ ይህ እንዲሆን ያስቻለው የባህር በሩን በመጠቀም ከየሀገራቱ ጋር ሲደረግ የነበረው ጠንካራ ግንኙነትና የንግድ እንቅስቃሴ ነው ብለዋል።

በታሪክ አጋጣሚ ኢትዮጵያ የባህር በር ማጣቷን የገለጹት ተመራማሪው፤ ወራሪዎች ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ወደቦችን ዕቃ ከማጓጓዝ ባለፈ መሣሪያ ማከማቻ አድርገው ኢትዮጵያን ለመውጋት ተጠቅመውበታል። ይህም የባህር በር አለመኖር ከንግድ ልውውጥ ባለፈ የደኅንነትም ስጋት መሆኑን ያሳየ መሆኑን ገልጸዋል።

አሁን ላይ ኢትዮጵያ የሌሎች ሀገራትን የባህር በር ለመጠቀም ከፍተኛ ወጪ እንደምታወጣ ጠቁመው፤ ጠላት ቢመጣባትም የምትፈልገውን መሣሪያ ለማስገባት የወደቡን ባለቤቶች ፍቃድ ማግኘት ይጠበቅባታል። ፋሽስት ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረ ወቅት ጂቡቲ በፈረንሳይ ስር ስለነበረች ኢትዮጵያ በጂቡቲ ወደብ መሣሪያ እንዳታስገባ መከልከሏን በማሳያነት አንስተዋል።

እንደ ተ/ፕሮፌሰር አየለ ገለጻ፤ የባህር በር ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገትና ሉአላዊነት መረጋገጥ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር በሚኖራት ስምምነት የጋራ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ።

ዛሬ ላይ የኢትዮጵያ ጎረቤት ሆነው ወደቦችን የተቆጣጠሩ ሀገራት ሉዓላዊ ሀገራት ናቸው ያሉት ተመራማሪው፤ ወደብ ለማግኘት የምናደርገው እንቅስቃሴ ሌሎችን በሚያስከፋ መንገድ ሳይሆን የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ባደረገ መልኩ መሆኑን በአግባቡ ግንዛቤ መፍጠር እንደሚገባ ገልጸዋል።

# “ በጎታች ነገሮች ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ፕሮፌሰር አፈወርቅ ካሡ የኢንዱስትሪ፣ የምርምር ማእከላትና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ትስስር ላይ ያተኮረ የምክክር መድረክ ላይ ትናንት ባደረጉት ንግግር እንዳሉት፤ በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ፈተና ውስጥ ነው ያለችው። ሀገርን ከፈተና ማውጣት የምንችለው ሁላችንም ሥራችንን በትኩረት ስንሠራ ነው።

በመሆኑም በዙሪያችን የሚፈጠሩ ጎታች ነገሮች ከዋናው ዓላማችን እንዳያስቱን ተሰናስለን ሥራችንን ከሠራን ሀገር ካለችበት ፈተና እንድትወጣ የራሳችንን አሻራ ማሳረፍ እንችላለን ብለዋል።

የትምህርት ተቋማት ብቁ ዜጎችን የማፍራት ከፍ ያለ ሀገራዊ ተልእኮ መሸከማቸውን የጠቆሙት ፕሮፌሰር አፈወርቅ፤ የትምህርት ተቋማት ከኢንዱስትሪና የምርምር ማእከላትና ጋር የሚያደርጉት ትስስር በየዘርፉ ብቁ ዜጎችን በማፍራት ነጋችንን ውጤታማ ለማድረግ ትልቅ አቅም ይፈጥራል ሲሉ ገልጸዋል።

በየአካባቢው ልዩ ልዩ ችግሮች መኖራቸውን አስታውሰው፤ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንደየአካባቢው ሁኔታ የማኅበረሰቡን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ የግንዛቤ ፈጠራና የምርምር ሥራዎችን ማከናወን ይችላሉ። አካዳሚውም ከእነዚህ ተቋማት ጋር በቅርበት ለመሥራት ዝግጁ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ በኢትዮጵያ ሳይንሳዊ ባህልና ፈጠራን ባህል ማድረግን አልሞ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ጠቅሰው፤ የትምህርት ተቋማትም ዋነኛ ግባቸው ይህ ስለሆነ በአግባቡ ተቀራርቦ መሥራት ያስፈልጋል።

በተቋማት መካከል የሚደረጉ ጥምረቶች ተቋማት የተሰጣቸውን ተቋማዊ ተልእኮ ለመወጣት ትልቅ አቅም የሚፈጥር ነው ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ የእነዚህ ተቋማት እንቅስቃሴ ድምር ውጤት ደግሞ ኢትዮጵያን አንድ እርምጃ ለማሻገር ያግዛል። በመሆኑም ሁላችንም ያለንን ሀብትና እውቀት አስተባብረን በመሥራት ለኢትዮጵያ እድገትና ብልጽግና የድርሻችንን ጠጠር እናስቀምጥ ብለዋል።

ባለፉት ዓመታት የእነዚህን ተቋማት ትስስር ለማጠናከር በርካታ ተግባራት መከናወናቸውን አስታውሰው፤ አሁን ላይ ጉዳዩ አዋጅ ሆኖ የተቀመጠ በመሆኑ ሥራዎችን ለማሳለጥ ትልቅ አቅም ይሆናል። በመሆኑም በየተቋማቱ ያሉ የሰው ሀብት፣ እውቀትና ሀብት አስተባብሮ ውጤታማ ተግባራት ለማከናወን መትጋት ይጠበቅብናል።

የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ምሁራንን በማስተባበር ችግር ፈቺ የሆኑ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑን ጠቅሰው፤ በቀጣይነትም ከተቋማት ጋር ያለውን ትስስር በማጠናከርና ዘመኑ የሚፈልገውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ለሀገራዊ ሁለንተናዊ እድገት አቅም ለመሆን እንሠራለን ብለዋል።

# የወል እሴቶቻችንን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ባህል አለን። እነዚህ እሴቶች መሠረታቸው አማኝነት ነው” ይላሉ።

ኡስታዝ አቡበከር፤ ማህበረሰቡ ላይ በተለይ ወጣቱ ላይ የሚታዩ የመደማመጥና የመተባበር ክፍተቶች ሰፊ መሆናቸውን ይናገራሉ። ሆኖም አሁን ባሉት አባቶችና እናቶች እንዲሁም የሃይማኖት መሪዎች ቀደም ሲል የነበረውን የመደማመጥና የመከባበር ታሪክ የማስቀጠል ሥራ መስራት ቢቻል “የትናንቱን ማንነቶቻችንን፣ መንፈሳዊ ልዕልናችንን፣ በመሰማማትና በመከባበር ችግሮችን ፈትቶና አስታርቆ የተባላሸን አቅንቶ የነገውን መልካም አሳይቶ በይቅርታና በፍቅር የጋራ ሀገራችንን ተባብረን እንድንኖርባት ማድረግ ይቻላል” ይላሉ። ይህ ከሆነ ብዙ ችግሮች እንደሚፈቱ፤ መሰማማት እንደሚቻልና የበለጠ መቀራረብ እንደሚፈጠር ነው የሚያነሱት።

በሀገር ሠላም ውስጥ ትልቁ ድርሻ የመከባበርና መሰማማቱ እሴት እንዲሁም የሽምግልና ባህል መሆኑን በመጥቀስ፤ በሠላም ግንባታ ሂደት የአባቶች ሚና ጎልቶ እንዲታይ፣ የወል የሆኑ እሴቶች የበለጠ እንዲጎለብቱ መንግሥትን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ትልቅ ሥራ እንደሚጠበቅባቸውና፤ ወደፊት እንዲመጡ ማገዝና መደገፍ እንደሚገባም ኡስታዝ አቡበከር ይናገራሉ።

ሁሉ ነገር በአስተዳደራዊ ውሳኔና ተቋማዊ አቅጣጫ አይፈታም የሚሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ እርስ በእርስ በሚያስተዋውቅ ማንነትና መገለጫዎች ችግሮች ሊፈቱ እንደሚችሉ ያመላክታሉ። በተለይም የፀጥታ መደፍረስ ሁሉንም ሰው እየጎዳና ዋጋ እያስከፈለ በመሆኑ የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች ማንንም ሳይጠብቁ ሀገርን የማስቀጠል ኃላፊነት እንዳለባቸው ይናገራሉ።

የቱለማ አባ ገዳና የኦሮሞ አባገዳዎች ህብረት ጸሐፊ አባ ገዳ ጎበና ሆላ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘመናት ሂደት ውስጥ የሚተዳደርበት፣ የሚከባበርበት፣ አብሮነትን የሚገልጽበት፣ ለሰላም፣ ለሀገር ሉዓላዊነትና አንድነት ተቻችሎና ተከባብሮ የሚኖርበትን የተለያየ እሴት የገነባ ነው ይላሉ።

ሕዝቡ ለሀገሩ ሉዓላዊነት መከበር የሚጠቀምበት የጋራ እሴት እንዳለው የሚገልጹት አባ ገዳ ጎበና፤ የተለያዩ የሃይማኖትና የሀገር ባህላዊ ክዋኔዎች ለአብሮነት ሲያገለግሉ እንደነበረም ይጠቅሳሉ። ኢትዮጵያ በረጅም የታሪክ ጉዞዋ ዘመናትን አብረው የተሻገሩ የሕዝቦቿ የጋራ እሴቶች ለሉዓላዊነቷ መከበር ትልቅ አስተዋጽኦ እንደነበራቸው ያነሳሉ። በተለያዩ ጊዜያት የነበሩ መሪዎች ቢቀያየሩም የሕዝቦች አንድነትና መከባበር ያለ መሸራረፍ የቀጠለ መሆኑንም ነው የሚገልጹት።

ሕዝቡ፣ በሃይማኖት መሪዎችና ታዋቂ ግለሰቦች፣ እንዲሁም በሀገር ሽማግሌዎች አማካኝነት ችግሮች ወደ ከፋ ደረጃ እንዳይደርሱ የማድረግ ልምድም ያለው ነው ይላሉ። ይህንን ለረጅም ዘመናት የቆየ የጋራ እሴት ዛሬም ተግባራዊ በማድረግ ለሀገር ሰላም ግንባታ ማዋል ይኖርባቸዋል ሲሉ ነው አባ ገዳ ጎበና የሚገልጹት። ሕዝቡ በፖለቲከኞች ሳይጠልፍ መቻቻል፣ መከባበርና ሀገርን መውደድ የሚገለጽበትን የጋራ እሴት በተጨባጭ በማሳየት አሁን ላይ በየቦታው የሚስተዋሉ ችግሮችን መፍታት ይኖርበታል በማለት ይናገራሉ።

የጋራ እሴትን ለሀገር ሰላም ግንባታ መጠቀም ከተቻለ የኢትዮጵያ ሰላም እንዳይረጋጋ የሚያደርጉ፣ አንድነቷ እንዳይጠበቅ የሚገፋፉና አብሮነት እንዲሻከር የሚጥሩትን ኃይሎች በቀላሉ ማሸነፍ እንደሚቻልም ይጠቅሳሉ። ለዚህ ደግሞ የሀገር ሽማግሌዎች ይቅርታንና ሀገርን የማስቀደም እሴትን በማስረጽ ለሀገሪቷ ሰላም መጠናከር የበኩላቸውን ኃላፊነት መወጣት እንዳለባቸው ይመክራሉ።

“የሰላም እጦቱ ሕዝቡን ጎድቷል፤ ኢኮኖሚውን ወደ ኋላ ጎትቶታል። ለሀገር ሰላምና አንድነት ሲውሉ የነበሩ የጋራ እሴቶች ዛሬም በተጨባጭ መሬት ወርደው መታየት ይኖርባቸዋል። የጋራ በሆነው ቃላችን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ፤ ሀገራችን የጋራ ቤታችን ነች ማለት የምንችለው ሰላም ሲኖር ነው። ይህንን ሰላም ማምጣት የምንችለው ደግሞ በትውልድ ቅብብሎሽ ያገኘነውን የመከባበር የጋራ እሴቶችን በመጠቀም ነው” ይላሉ።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የደህንነት ቋሚ ኮሚቴ አባል አምባሳደር ዲና ሙፍቲ በበኩላቸው፤ ብዝኃነትን የሚያስተናግዱ ሀገራት ችግሮች ባጋጠማቸው ወቅት የጋራ እሴቶቻቸውን ተጠቅመው እንደሚፈቱ ይገልጻሉ። በኢትዮጵያ እዚህም እዚያም የሚስተዋሉ ችግሮችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስወገድም ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ ወደ ሥራ መግባቱን በመጥቀስ፤ ይህም ጦርነትን መሠረት ያደረገ መፍትሄ አስፈላጊ ባለመሆኑ ልዩነቶችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል ትልቅ ሥራ እንደሆነ ይናገራሉ።

የተጣሉ የሚታረቁበት፣ አብሮነት በጉልህ የሚንጸባረቅባቸው የጋራ እሴቶች በርካታ ናቸው ያሉት አምባሳደር ዲና፤ ህብረተሰቡ ተሳትፎ ሲያደርግ ችግሮችን ለመፍታት የቆዩ ሀገራዊ የጋራ እሴቶችና ልምዶች ቀምሮ ወደ ተግባር መግባት እንደሚያስፈልግ ይጠቁማሉ። ይህ እንዲሳካም የኅብረተሰቡ ተሳትፎና ሚና ከፍተኛ መሆን እንዳለበት ይጠቁማሉ።

ተናጋሪዎቹ፤ እንደ ሀገር የጋራ እሴት ባለቤት መሆን እድለኝነት መሆኑንና የወል እሴቶችን በመከተል ነገን ማስተካከል እንደሚገባ ጠቅሰው፤ በዚህ መንገድ ካልተሰራ ግን ለሚፈጠሩ ችግሮች ሁሉም ሰው ከተጠያቂነት እንደማይድን ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሽግግር ፍትሕ ወደ ሰላምና ልማት ለሚደረገው ጉዞ ትልቅ አቅም ነው !

የሀገራችንን ታሪክ መለስ ብሎ ላጤነው የውስጥ አለመግባባት፤ ግጭትና ጦርነት የበዛበት ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን በጋራ ታሪኮቻችን ዙሪያ የጋራ መግባባት ላይ አለመድረሳችን እንደ ሀገር በማያባራ የግጭትና የጦርነት አዙሪት ውስጥ ለመግባት ተገደናል። በዚህም በየወቅቱ ለበርካታ ሰብዓዊ ጉዳትና ቁሳዊ ኪሳራ ተዳርገናል።

በየወቅቱ በተካሄዱ ግጭቶችና ጦርነቶች ምክንያት ከፍ ላሉ ሰብዓዊ ጉዳትና ቁሳዊ ወድመቶች ከመጋለጣችንም ባለፈ፤ ለከፋ ድህነትና ኋላቀርነትም ተዳርገናል። በዚህም በብዙ መልካም ስሞች በዓለም አቀፍ ደረጃ የመጠራታችን ያህል፤ አንገት በሚያስደፉ የምግባር መገለጫ ስሞች እንድንጠራም የግድ ብሎናል። ሁሉ እያለን በጠባቂነት ተርታ እንድንሰለፍ ሆነናል።

ይህንን እውነታ ለመለወጥ በተለያዩ ወቅቶች ጥረት ቢደረጉም፤ የሚጠበቀውን ያህል ፍሬ ሊያፈሩ አልቻሉም። በተለይም የሀገሪቱ የፖለቲካ ለውጦች በኃይልና በሴራ ላይ የተመሰረቱበት መንገድ /ባህል ጥረቶቹ ፍሬ አፍርተው ሀገሪቱ እንደ ሀገር ካለችበት የግጭት አዙሪት መውጣት ሳትችል እንድትቀር አድርገዋታል።

ይሁን እንጂ የ2010ሩ ሀገራዊ ለውጥ ይሄንን የፖለቲካ መንገድ ወደ አዲስ ምዕራፍ የለወጠ ሆኗል። ሁሉን አጥፍቶ ከዜሮ የመጀመር አባዜን አስቀርቶ፤ መጥፎውን አርሞና መልካሙን አጎልብቶ የሚራመድ አዲስ የሪፎርም አካሄድን በኢትዮጵያ አስተዋወቀ። በሁለንተናዊ ብልጽግና እውን የማድረግ እሳቤ ውስጥም የሕግ የበላይነትን ማስፈን፤ ፍትህን ማረጋገጥም ትኩረቱን አደረገ።

ይሄን ያስተዋወቀው የለውጡ መንግሥት ታዲያ፣ ለጀመረው ሁሉን አቀፍ ልማት ከሁሉም በላይ ዘላቂ ሰላም ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ፣ ሀገራዊ አለመግባባቶችን በድርድርና በውይይት መፍታት የሚያስችል የአስተሳሰብ መሠረት ለመጣል ረጅም መንገድ ተጉዟል። ችግሮችን በይቅርታ ለማለፍ ከመሞከር ጀምሮ ለውጡን በመተማመን ለማስቀጠል ጥረት አድርጓል።

የሕግን የበላይነት እውን ለማድረግ እና ፍትሕን በማጽናት ዜጎች በፍትህ ሥርዓቱ እንዲታመኑ፣ በተለይም በተለያዩ አጋጣሚዎች ለተለያዩ ሰብዓዊ መብት ጥሰት ሰለባ የሆኑ ዜጎች ተገቢውን ፍትህ እንዲያገኙ የሽግግር ፍትህ ተግባራዊ የሚሆንበትን አስቻይ ሁኔታ በማመቻቸት ለፍትሃዊነት ያለውን ቁርጠኝነት በተጨባጭ አሳይቷል።

ለዚህም ሲባል ህዳር 15 ቀን 2015 ከፖሊቲካ ጣልቃ ገብነትና ከተጽዕኖ ነጻ በሆነ መልኩ የሽግግር ፍትህ ከፍተኛ የባለሙዎች ቡድን እንዲቋቋም አድርጓል። ቡድኑ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና የተባበሩት መንግሥታት ከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የጋራ የሰብዓዊ መብቶች የምርመራ ውጤት ምክረ ሃሳብን እንዲሁም ጥቅምት 2015 የተደረገውን የፕሪቶሪያ ስምምነት ላይ በመመሥረት ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል።

በእስካሁኑ ሂደት የሽግግር ፍትህ የባለሙዎች ቡድን 47 ክልላዊና 8 ሀገር አቀፍ የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮችን ጨምሮ፤ 9 በልዩ ሁኔታ በተለያዩ የማሕበረሰብ ክፍሎች ላይ ያተኮሩ የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮችን ከተባበሩት መንግሥታት የተለያዩ ቢሮዎች፤ ከአፍሪካ ሕብረት፤ ከኢጋድ፤ እና ከሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በቅንጅት አከናውኗል። በ12 ክልሎችና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች በመድረስ ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር ውይይቶችን አካሂዷል።

ውይይቶቹ በኢትዮጵያ ያለውን ብዝሃነትና ልዩነት ባማከለ፤ በሰብዓዊ መብቶች መርህ ላይ የተመሠረቱና ተጎጂዎችን ማዕከል ባደረገ መልኩ የተከናወኑ ናቸው። ከከተሞችና ከአጎራባች አካባቢዎች የመጡ የተለያዩ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ሰለባዎችን፤ በሀገሪቱ ውስጥ የተጠለሉ ስደተኞችን ጨምሮ ተፈናቃዮችን፤ አካል ጉዳተኞችን፤ ሕጻናትን፤ የመሳሰሉ የተገለሉ የማሕበረሰብ ክፍሎች ያሳተፈ ነው።

የምምክር ሂደቱ በሁሉም መድረኮች ቢያንስ 40 በመቶ የሚሆኑት ተሳታፊዎች ሴቶች እንዲሆኑ አድርጓል። ይህ ደግሞ በተለይም በጦርነትና በግጭት ወቅት ግንባር ቀደም ተጎጂ የሚሆኑት ሴቶች በመሆናቸው በተለያዩ ወቅቶች በሴቶች ላይ እየደረሱ ያሉ ጥሰቶች ጎልተው እንዲወጡ ያስችላል።

ከቋንቋ አንጻርም ብዝሃነትን ባማከለ መልኩ በሁሉም ቋንቋ ውይይቶች እንዲካሄዱ ተደርጓል። ይህም ተጎጂዎች ሃሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹና ደረሰብኝ የሚሉትን ችግር በቀላሉ እንዲያስረዱ አስችሏቸዋል። በዚህም ሕብረተሰቡ በጉዳዩ ላይ የነቃ ተሳትፎ ከማድረጉም በተጨማሪ በጉዳዩ ላይ የባለቤትነት መንፈስ እንዲያዳብር አስችሏል።

በአሁኑ ወቅት የሽግግር ፍትህ የምክክር መድረክ የማጠናቀቅ ሂደት ላይ ይገኛል። የሽግግር ፍትህ እውን መሆንም እንደ ሀገር ያለመግባባት፣ የግጭትና የጦርነት ታሪካችን ተዘግቶ በጋራ ታሪኮቻችን ላይ የምንግባባ፤ ለጋራ ሀገራችን የምንተጋ፤ ለልጆቻችንም የበለጸገች ኢትዮጵያን ለማውረስ የሚያስችል ነው።

በተለይም ለመጀመሪያ ጊዜ በሚባል መልኩ ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነትና ከተጽዕኖ ነጻ የሆነ የሽግግር ፍትህ የባለሙዎች ቡድን ተቋቁሞ ወደ ሥራ መገባቱ አጥፊዎች የሚጠየቁበትን፤ ተጎጂዎችም የሚካሱበትን አሠራር ተግባራዊ እንዲሆን ያስችላል። በቀጣይም ተመሳሳይ ጥፋቶች እንዳይደገሙ ትምህርት ይሰጣል።

የምክክር ሂደቱም ተጎጂዎችን ማዕከል ባደረገ መልኩ መካሄዱም ፍትህ የሚሹ ወገኖች እንዲካሱ እና ዜጎች በፍትህ ሥርዓቱ ላይ እምነት እንዲኖራቸው በር ይከፍታል። በሂደቱም የፍትህ ሥርዓቱ እንዲጠናከር መሠረት ይጥላል።

የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቆ የታለመለትን ግብ እንዲመታ የመላው ኢትዮጵያውያን ተሳትፎ ተጠናክሮ ሊቀጥል፤ በገንዘብ፣ በቴክኒክና በሃሳብ ድጋፍ እያደረጉ ያሉ አካላትም ተሳትፏቸውን አጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ሠላም ለቱሪዝም

**ምስጋና ፍቅሩ**

ኢትዮጵያ እጅግ ብዙ ታሪክ፣ ቅርስ ፣ባህል ፣ የተፈጥሮ ፀጋ የተቸራት ፤ምድሯም በሚያማምሩ አዕዋፋት እና በብርቅዬ የዱር እንስሳት የደመቁ ፤ ሀገር ነች። ከዚህ በተጨማሪም እንደ ጥምቀት፣ መስቀል፣ ፍቼ ጨምባላ እና ኢሬቻ ያሉ ኃይማኖታዊ እና ባህላዊ ኩነቶች ደምቀው የሚከበሩባት የተለያየ ኃይማኖቶችና ባህሎች መገኛ ናት ።

እነዚህ ተፈጥዊ ፣ኃይማኖታዊ እና ማህበራዊ ውበቶች ሀገሪቱ በብዙ መልኩ ለቱሪዝም ዘርፍ ተመራጭ የሚያደርጓት ናቸው ። ዘርፉ የአንድን ሀገር በኢኮኖሚ ከመደገፍ አንጻር ካለው አበርክቶም ሀገሪቱ ለጀመረችው ልማት ትልቅ አቅም እና ተስፋ እንደሚሆን ይታመናል።

እንኳን እንደ ኢትዮጵያ በባህል፣ በኃይማኖት፣ በታሪክ፣ በብርቅዬ እንስሳት እና በብዝሃነቷ የታደለችን ሀገር ቀርቶ፤ እዚህ ግባ የሚባል ታሪክ፣ ባህል እና ቅርስ የሌላቸው ሀገራት ሠው ሰራሽ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን በመሥራት ብሎም ጎብኚዎችን በመሳብ ከፍተኛ የሚባል ገቢ እያገኙ እንደሆነ እሙን ነው።

ዘርፉ ለአስጎብኚዎች የሥራ ዕድልን በመፍጠር፣ የሆቴል ዘርፉን በማሳደግ ፣ የቱሪስት መዳረሻ አካባቢ ያለው ማህበረሰብ በሁለንተናዊ መልኩ ተጠቃሚ በማድረግ ለሀገር ኢኮኖሚ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍያለ ነው።

> ❝ ዘርፉ ለአስጎብኚዎች የሥራ ዕድልን በመፍጠር፣ የሆቴል ዘርፉን በማሳደግ ፣ የቱሪስት መዳረሻ አካባቢ ያለው ማህበረሰብ በሁለንተናዊ መልኩ ተጠቃሚ በማድረግ ለሀገር ኢኮኖሚ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍያለ ነው ❞

በተለይም እንደ ሀገር ያሉንን ተፈጥሯዊ ታሪካዊ፣ ኃይማታዊ እና ባህላዊ ቅርሳችንን ማልማትና በዓለም አቀፍ ደረጃ በስፋት ማስተዋወቅ ከቻልን አሁን ላይ ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ለጀመርነው ሀገር አቀፍ ጥረት የሚኖረው አበርክቶ ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል።

በተለይም እንደ ሀገር ያለን የቆየና በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኘው የእንግዳ ተቀባይነት ባህላችን በራሱ ዘርፉን ስኬታማ ለማድረግ ለምናደርገው ጥረት የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ከዚህ አንጻር አሁን ላይ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚታየው የጸጥታ ችግር የእንግዳ ተቀባይነታችን ባህል እንዳይበርዘው ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

በሀገራችን በአራቱም አቅጣጫ ያሉ የቱሪስት ዓይን የሚስቡ በርካታ የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶች ትርጉም ያለው የኢኮኖሚ አቅም የሚሆኑት አሁን አሁን እየታየ ያለውን የጸጥታ ችግር አግባብ ባለው መልኩ ለዘለቄታው መፍታት ሲቻል ነው።

አሁን ላይ ያለው የጸጥታ ችግር በቱሪዝም ዘርፉ ላይ እያሳደረ ያለውን ችግር ሃላፊነት እንደሚሰማው ዜጋ በማጤን ፈጥኖ ማረም ያስፈልጋል። ይህን ማድረግ ከተቻለ ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ የተጀመሩ ሆኑ የታሰቡ ሥራዎች ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉም።

ከቦታ ወደ ቦታ በሰላም መዘዋወር ፈተና እየሆነ የመምጣቱ ጉዳይ የውጭ ቱሪስቶችን ብቻ ሳይሆን በሀገር ውስጥ በዜጎች የሚደረጉ ፤ ለዘለቄታው መለመድ ያለባቸው ፤ አካባቢዎችን የመጎብኘት ባህል ሊያዳክሙት ይችላሉ።

በእርግጥ አሁን ላይ በዘርፉ በርካታ በጥሩ ጎን ሊጠቀሱ የሚችሉ ሥራዎች እየተመለከትን እንገኛለን። የቱሪዝም ዘርፍ ሚናው የጎላ መሆኑን በመረዳት ከመስከረም 29 እስከ ጥቅምት 28 ቀን 2016 ዓ.ም በሳይንስ ሙዚየም ‹‹ሀገር አቀፍ የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ አውደ ርዕይ›› መከፈቱ እየተሠሩ ካሉ ሥራዎች መካከል ተጠቃሽ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አውደ ርዕዩን መርቀው ሲከፍቱ እንደተናገሩት ፤ አውደ ርዕዩ ጎብኚዎች ኢትዮጵያን ምቹ መዳረሻ የሚያደርጋትን በናሙና እንዲያዩ ዕድል ይሰጣል።

“በዘርፉ ያለንን አቅም ለማውጣት፣ ኢትዮጵያን የብዙ ውበቶች እና ግኝቶች መዳረሻ አድርጎ ለማስተዋወቅ እና ለማገልገል ሁሉም ኢትዮጵያውያን ሀገራቸው ያላትን ሀብት ማየት፣ ማውጣት፣ ማስተዋወቅ እና ማገልገል ይጠበቅባቸዋል ።”

እንዲህ አይነት አውደ ርዕይ ሀገሪቱ በዘርፉ ያላትን ፀጋዎች ይበልጥ ለማስተዋወቅና የዘርፉን ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ዕድል እንደሚፈጥር በመገንዘብ፤ መሰል መሰናዶዎችን ማዘጋጀት እና በችግሮቹ ዙሪያ እንዲሁም ለችግሮቹ መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን በማጤን ቀጣይነት ያለው ሥራ መሥራት ያስፈልጋል።

ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ በበኩላቸው ለሁለቱ ምክር ቤቶች በቅርቡ ባደረጉት ንግግር እንዳሉት ፤ “የቱሪዝም ዘርፍ የዕድገት አማራጭ አንዱ ቁልፍ ዘርፍ ነው። በዚህ በኩል በዓመቱ የቱሪስት ፍሰቱን በማሳደግ በኩል ፈታኝና አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ አበረታች ዕድገት ለማስመዝገብ ጥረት መደረጉን በጥንካሬ ማንሳት ተገቢ ነው።”

በአዲስ አበባ እየተሠሩ ያሉ እና የከተሜውንም ሆነ የውጭ ሀገሩን ጎብኚ ቀልብ ሊስቡ የሚችሉ ፕሮጀክቶች በስፋት እየተመለከትን እንገኛለን። ይህም በእለት ተእለት እንቅስቃሴው ለሚደክመው የከተሜው ሕዝብ፤ ዓይን ማረፊያ ማግኘት መቻሉ መንግሥትን የሚያስመሰግነው ነው። እንደነዚህ ያሉት ፕሮጀክቶች በስፋት መሠራቱም፤ በብዙ ነገር ለታደልነው ሕዝብ ሌላ እሴት የሚጨምር መሆኑን መገንዝብ ያሻል።

እኛ ኢትየጵያውያን የተሰጠን የተፈጥሮ ፀጋ ብዙ ነው። ነገር ግን ይህንን የታደልነውን ነገር በመጠቀም ሆነ ሌሎች እንዲያውቁት ከማድረግ አንጻር ግን ክፍተታችን ብዙ ነው። በአካባቢያችን ሊጎበኙ የሚችሉትን እንኳን አቅሙ እያለንን እና ሁኔታዎች አመቺ ሆነው ፍላጎታችን ዝቅተኛ ነው።

የውጭ ጎብኚውን ለመሳብ ጥረት እንደሚደረገው ሁሉ፤ በተለያዩ ሁነቶች ላይ ለመታደም ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው ክልል የሚንቀሳቀሰውን የሀገር ውስጥ ጎብኚውን በስፋት የማሳተፍ ሥራ መሥራት ከዘርፉ ተዋናዮች አሁን ላይ የሚጠበቅ ትልቁ ሥራ ነው ።

ዘርፉ ውጤታማ እንዲሆን በበጀት፣ የተሟላ መሠረተ ልማት፣ የሠው ኃይል፣ ምቹ አካባቢ እና ከሁሉም ከሁሉም ሠላም የሰፈነበት ከባቢ ካለው፤ ትርፋማ ለመሆን የሚያግደው ነገር የለም ። ከላይ የጠቀስናቸው እንዳሉ ሆነው፤ የቱሪዝም ዘርፉ ውጤታማ እንዲሆን እና ሀገሪቱም ከዘርፉ የምታገኘውን ገንዘብ ለማሳደግ ስለ ሠላም የጊዜ ቀጠሮ ሳይሰጠው ሊሠራ ይገባል።

በተጨማሪም የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) የተመዘገቡ የማይዳሰሱ እና የሚዳሰሱ ቅርሶችን መንከባከብ እና መጠበቅ ግድ ይላል። በተለይ በግጭቶች ወቅት ለነዚህ ቅርሶች ከፍ ያለ ጥንቃቄ ማድረግ እና ከየትኛውም አይነት ስጋት ነጻ መሆናቸውን ማረጋገጥ የሁሉም ዜጋ ሃላፊነት ነው።

# ነፃ ሃሳብ

# እርቅ ሀገር የሚያንጽ የትውልድ ድልድይ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

በሀገራችን እርቅ የሚያሻቸው ብዙ ጉዳዮች አሉ። ከትናንት የመጡ፣ ዛሬ የተፈጠሩ ፤ ታሪክ አጣመው፣ እውነት አዛንፈው ትርክት በፈጠሩ ራስ ወዳድ ግለሰቦችና ቡድኖች የተፈበረኩ የልዩነት ቁርሾዎችም ጥቂት አይደሉም። እኚህንና መሰል የትውልዱን መረማመጃ የዘጉ የጥፋት ሃሳቦች እንዲወገዱና በምትኩ አዲስ የፍቅርና የእርቅ መረማመጃ እንዲሠራ ሀገር የሚያንጽ እርቅ ያስፈልጋል ።

ሀገር ብዙ እጆች ከብዙ ሃሳብ፣ በብዙ ጥበብ አላቁጠው የሠሯት ነች ። ይቺ በብዙ ሃሳብ ከብዙ ጥበብ ተላቁጣ የተሰራች ሀገር ሰፊና ጥልቅ፣ ብዙሃነትን የለበሰች ነች ። በዚህ እሳቤ እንደ ሀገር ከተሠራንበት አብሮነት የመለያየት ሃሳብ እንዴት ገባብን? የዚህ ርዕስ ጥያቄ ነው።

ከሥነምግባርና ከግብረገብነት እንዲሁም ደግሞ ከአብሮነት አንጻር ኢትዮጵያን ድሮና ዘንድሮ ብለን ብንመለከታት ሁለት አይነት ማንነቶችን እናገኛለን። የበፊቱ ትውልድ ኢትዮጵያዊነትን ሲገልጸው የታሪክና የአብሮነት ውህድ ብሎ ነው። የአሁኑ ትውልድ ይሄን ስም ሲፈታው.. እኔና የእኔ ብሎ ነው። በእኚህ ሁለት ፊትና ኋላ አረዳዶች ውስጥ ጸጋውም ሆነ መርገምቱ የሚያርፈው በሀገርና ህዝብ ላይ ነው።

‹እኔ እና እኛ› ትናንትም ሆነ ዛሬ ዓለምን ለሁለት የገመሱ እዛና እዚህ የሚረግጡ አመለካከቶች ናቸው። እኛ ስንል ብዙሃነትን ከማስታወስ ጎን ለጎን ለጋራ ታሪክና ለጋራ እሴቶች እውቅና እየሰጠን ነው። ሰላምና አንድነትን መቻቻልንም እየሰበክን ነው። በኢትዮጵያዊነት ውስጥ ያሉ በወርቅ ምንጣፍ ላይ ያራመዱንን የወንድማማችነት ፈለጎችን እየገለጥን ነው። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ የሕግ ሁሉ በኩር፣ የሥርዓት ሁሉ መነሻ የሆነውን ፍቅር ለትውልዱ እያስቀመጥን ነው።

እኔ ስንል ግን ከሰፋና ከገዘፈ ህብረብሄራዊ ማንነት ውስጥ አንድ ነጠላ እውነት መምዘዝ ነው። በፍቅርና በአብሮነት የተገነባውን ኢትዮጵያዊነት ሌላ ባዕድ መልክ መስጠት ነው። የጽናትና የአይበገሬነት ምሳሌ የሆነውን ብዙሃነት ማደብዘዝ ነው። ፍቅርን ምንድነህ ፣ አብሮነትን ወዲያ ሂድ እንደማለት ነው። ከፍ ሲል ደግሞ ትውልዱን ጥላቻና ራስ ወዳድነትን ማስተማር ነው። ትውልድ ፍቅር ያልወረሰባት ሀገር ደግሞ ከመደማማት በስተቀር ምንም መዳኛ የለውም ። ከዚህ አንጻር እንደመጣንበት እና እንደወረስነው ታሪክ እኛ ብለን ጀምረን እኛ ብለን የምንጨርሰው አሁናዊ የጋራ ተግባቦት ያስፈልገናል።

ሀገር ትናንትና ዛሬ በትውልዶቿ በኩል የተለያየች ናት። ጀግና ትውልድ ሁልጊዜም መነሻው ፍቅር ነው። ፍቅር የገባበት፣ እርቅና ተግባቦት ያለበት ፖለቲካና ማህበራዊ መስተጋብር ለትውልዱ ትልቅ እድል ይዞ የሚመጣ ነው። የዚህ ትውልድ ሰፋፊ አዳራሾች አነጋግረው የሚያግባቡ፣ አደማምጠው አንድ የሚያደርጉ መሆን አለባቸው።

የእኛ ድምጽ ወደ ነገ የሚሄድ ነው። የእኛ ፖለቲካ፣ የእኛ ንግግር ሩቅ የሚሰማ ነው። ማንም አይሰማንም ብለን በሹክሹክታና በለሆሳስ ያወራነው እንኳን ለሌላው ጆሮ የሚሰማ ነው። ማንም አየኝ አላየኝ ሳንል ከእኛ የሚጠበቀውን በጎ ነገር ማድረግ ብንችል ብዙ የምንቀርፋቸው ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተግዳሮቶች ነበሩ።

ትውልድ ሂደት ነው። በአንድ ጊዜ የሚሆን አይደለም። ግን ዛሬ ላይ በምንሆነው በየትኛውም ነገር እየተፈጠረ እና እያደገ የሚሄድ ነው። አሁን ላይ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የምናደርገው የትኛውም ነገር በትውልዱ አእምሮ ውስጥ ወደነገ የሚሄድ ነው። ዝግ ያልን ቢመስለንም ከፖለቲካና ከብሄር ሽኩቻችን ጋር ወደነገ እየሄድን ነው። ዝግ ያልን ቢመስለንም ከጥላቻና ከእኔነታችን ጋር ወደ ፊት እየገሰገስን ነው።

> መድረኮቻችን እንደዚህ ቀደሙ አውርተንና ተሳስቀን ወይም ደግሞ አድማጭና ተናጋሪ በሆነ ሁናቴ ገብተን የምንወጣባቸው ሳይሆኑ ለችግሮቻችን የመፍትሄ ሃሳቦች የሚመነጩበት፣ መሰል ችግሮች እንዳይደገሙ መንገድ የምንዘጋበት ነው። አዲስ ልምምድ ይሄ ነው። ከዚህ ቀደም ያለአንዳች ተግባቦት ገብተን የወጣንባቸው፣ ተሰብስበን የተለያየንባቸው ብዙ መድረኮች አሉ። በጋራ ጉዳይ ላይ አድማጭና ተናጋሪ የለም

አሁን ላይ ቆመን ስለፍቅር አንድ ወንበር ላይ ካልተቀመጥን፣ ባማሩ ባዶ አዳራሾቻችን ውስጥ ስለአብሮነት ካልተሰበሰብን ትውልዱን እየበከልነው ነው። በርግጥ ከየትኛውም ሀገርና ህዝብ በላይ የአብሮነት ታሪክ ያለን ህዝቦች ነን። ዓለምን ለአፍታ ብንቃኛት የእኛን ያክል የተደባለቀና የተሰናሰለ ታሪክና ትውፊት፣ እምነትና እውነት ያለው ህዝብ የለም። ከዚህ ውስጥ መውጣት አይቻልም። የሚበጀን እንዳነሳሳችን አብሮ መቀጠል ነው። የሚጠቅመን ኢትዮጵያን ከፊት አድርጎ መከተል ነው። አብሮ ከመውደቅና ታሪክ አልባ ከመሆን ባለፈ ግፊያ ማንንም ፊተኛ፣ ማንንም በኩር አያደርግም።

እንደ ሀገር ሀገር ስንሆን፣ እንደ ህዝብ ህዝብ ስንሆን ያማረብን ምን ነበር? በተጋመዱና በተጠላለፉ እጅና ክንድ የተጠላለፈ ታሪክ ስናበጅ ያማረብን ምን ነበር? ለክብርና ለነጻነት ስንታገል፣ ከነጭ አገዛዝ ስንወጣ፣ ለሰብዓዊነት ስንተጋ ያማርነው እንዴት ነበር? በአንድነት ልቀን በዓደዋ ጀብድ ስንጽፍ፣ በአብሮነት ደምቀን ኢትዮጵያዊነትን ስናስጠራ መነሻችን ምን ነበር? የሚሉትን መጠየቅ ተገቢ ነው ።

ከጋሞ ዮ መስቀላ፣ ከወላይታ ጊፋታ፣ ከሲዳማ ጨምበላላ መዐድ ስንቀርብ፣ በሴራ እና በያአዴ፣ በኤሬቻና አሸንዳ ሶለን ፊት በወንድማማች ስንቆም ያበረታን ምን ነበር? በመስቀል ፋሲካው፣ በኢድና አረፋ ተያይዘን ስንመጣ፣ ተቀራርበን ስናወጋ ጥበባችን ምን ነበር? ከራቀ ትናንት ወደዛሬ ስንመጣ፣ ከቀረበ አሁን ወደ ራቀ ነገ ስንሄድ በምን ተሳፍረን፣ ምንን ተስፋ አድርገን ነው? መልሱ ፍቅር ነው.. መልሱ አንድነት ነው።

ኢትዮጵያዊነትን በዚህ ልክ ያገነነው ፍቅር ነበር። በዚህ ልክ እንድንበረታና እንድንጠነክር ያደረገን አብሮነት ነበር። አሁንም ፍቅር ነው የሚያስፈልገን። ተቀራርቦ እንደመወያየት፣ ተወያይቶ እንደመስማማት ታላቅ ጥበብ የለም። ብዙዎች ጥበብን ያልሆነ ቦታ ይፈልጉታል። ታላቁ ጥበብ ያለው ከሰው ልጆች ጋር በጋራ መኖር ውስጥ ነው። ይሄ እውነት በታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ ላይም ሳይቀር ሰፍሮ ይገኛል።

ፍቅርን የሕግ መጀመሪያ፣ የሥርዓት ፊተኛ ያላደረገ ሀገርና ህዝብ፣ ፖለቲካና ፖለቲከኛ በምንም ቢበረታ መዛሉ አይቀርም። አጀንዳችንን ፍቅር አድርገን ለእርቅ ስንቀመጥ ብቻ ነው ፍሬ የምናፈራው። ጉዳያችንን ሀገርና ህዝብ አድርገን ስንሰበሰብ ብቻ ነው በልዩነቶቻችን ውስጥ የጋራ አቋም የሚኖረን። ፍቅር ማሸነፍ አይደለም። ፍቅር ልክ የሚሆነው በመሸነፍ ውስጥ ነው። የኛ ፖለቲካ ደግሞ የለመደው ማሸነፍን ነው። የእኛ ጭንቅላት የተለማመደው ጥሎ ማለፍን ነው። ማሸነፍን ሽተን የምንቀመጥ ከሆነ እርቅና ስምምነት አይመጣም።

ትውልዱ ሳይገፋፋ፣ ፖለቲከኞቻችን ሳይጠላሉ የሚሄዱበት የፍቅር ድልድይ መገንባት አለበት። በእርቅ ደማችንን ካላደረቅን ወደፍቅር መቅረቢያ ሌላ መንገድ አናገኝም። አባቶቻችን ሲያስታርቁም ሆነ ሲምሩ ‹ይቅር ለእግዜር› ብለው ነው። አማኝ ለሆነ ማህበረሰብ ፍቅርና ይቅርታ ማህበራዊ እሴቶች እንጂ በል ተብለው የሚባሉ ሃይልና ግዴታ የሚያሻቸው ነገሮች አይደሉም። በአንድነት መዐድ ፊት በአንድ የበላንባቸው ፎሌዎቻችን፣ በአንድ የጠጣንባቸው ሽክናዎቻችን ታሪክ አውሪ ከመሆን በላይ ለዛሬ መቧደናችን መልስ የሚሰጡን ናቸው።

ብዙ ታሪክ፣ የተለያየ ህዝቦችና እሴቶች ባላት ሀገር ውስጥ ነን። ልዩነታችን ከአንድነታችን አይበልጥም፣ በልጦም አያውቅም። ኢትዮጵያ ሰፊ ግዛት ናት። ባህሏ፣ ተፈጥሮዋ፣ መልካምድሯ፣ ሥርዓቷ፣ ወግ ልማዷ በፍቅር ለሚኖሩ የበቃ ነው። በፍቅር ካልሆነ ግን ሀገር ጠባብ ናት። ሁላችንንም የሚያግባባ አንድ እውነት ቢኖር ጥላቻ መልካሙን የሚያከፋ፣ ሰፊውን የሚያጠብ መሆኑ ነው። የሚያምርብን ፍቅር ነው። በአንዳንድ አለመግባባት የወየበው አብሮነታችን እንዲመለስ ልባችንን ከጥላቻ አጽድተን ለዳግም ትንሳኤ መቀመጥ ከእንዳንዳችን የሚጠበቅ አሁናዊ ግዴታ ነው።

አበው ሲተርቱ ‹እርቅ ደም ያድርቅ› ይላሉ። እውነት ነው እርቅ ደም የሚደርቅበት፣ ፍቅር የሚመለስበት መድረክ ነው። የትኛውም መቆሳሰል፣ የትኛውም መደማማት በእርቅ ካልሆነ አይሽርም። ትናንትና በህዝቦቿ ፍቅርና አንድነት ወንዝ የተሻገረችው ሀገር ዛሬ ጥላቻን ባነገቡ አመለካከቶች ከክብሯ እየተንሸራተተች ያለችበት ሁኔታ ስለመኖሩ ሁላችንም ምስክሮች ነን። ችግርን ከስሩ ከመቅረፍ ይልቅ የማሽሞንሞን ልማድ አለን። ያሽሞነሞናቸው ችግሮች ዛሬ ላይ ፈርጥመው ጥርሳቸውን አግጠውብናል። ችግርን ከስሩ የሚል አዲስ ልምምድ ያስፈልገናል።

ውሎ የሚያድር ችግር ውሎ የሚያድር መጨረሻ አልባ ተግዳሮት ነው ይዞ የሚመጣው። በምንም ይሁን ትናንት ላይ የተፈጠሩ የፖለቲካም ሆነ የሃሳብ ልዩነቶች ወደዛሬ መጥተው ዋጋ እያስከፈሉን ይገኛሉ። ወደነገ እንዳይሄዱና ሌላ ዋጋ እንዳያስከፍሉን ምንጫቸውን ማድረቅ ከእርቀ ሃሳብ ጎን ለጎን ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ነው። ፍቅርና አንድነትን ሊያዳብሩ የሚችሉ እንደ ውይይትና ምክክር ያሉ ትናንት ላይ ያልነበሩ አዳዲስ ህዝባዊ መድረኮች ያስፈልጉናል።

መድረኮቻችን እንደዚህ ቀደሙ አውርተንና ተሳስቀን ወይም ደግሞ አድማጭና ተናጋሪ በሆነ ሁናቴ ገብተን የምንወጣባቸው ሳይሆኑ ለችግሮቻችን የመፍትሄ ሃሳቦች የሚመነጩበት፣ መሰል ችግሮች እንዳይደገሙ መንገድ የምንዘጋበት ነው። አዲስ ልምምድ ይሄ ነው። ከዚህ ቀደም ያለአንዳች ተግባቦት ገብተን የወጣንባቸው፣ ተሰብስበን የተለያየንባቸው ብዙ መድረኮች አሉ። በጋራ ጉዳይ ላይ አድማጭና ተናጋሪ የለም። ሀገር በአንድ ሰው ሃሳብ ብቻ አትጸናም። ላሉብን ዘርፈ ብዙ ምስቅልቅሎች ዘርፈ ብዙ ህዝባዊ ተሳትፎ ያስፈልጋል። በሀገራችን ላይ ያየነው የሰማነው እንዲህ ቢሆን እንዲህ ይሆን ነበር ብለን የምናምነው የመፍትሄ ሃሳብ አለ። ያን ሃሳብ በመወርወር ከዛ ሃሳብ ጋር የተቧደኑ ሌሎች ሃሳቦችን በመፍጠር ነው ሀገር የምናረጋጋው።

‹ነገርን ከስሩ ውሃን ከምንጬ› እንዲሉ የዛሬዎቹ ወደ ነገ እንዳይሄዱ፣ የትናንቶቹም ዛሬ ላይ እንዲያበቁ ሁሉንም አይነት የተግባቦት አማራጭ ማየቱ ተገቢ ይሆናል። ባለን የፖለቲካ አረዳድም ሆነ ሁለንተናዊ ቅኝት ትናንትና ዛሬ የተለያየን ለመሆናችን ማስረጃ አያስፈልገውም። ብዙሃነትን ታቅፋ ላለች ዥንጉርጉር ሀገር ዋናው እና ወሳኙ ነገር ከልዩነት በፊት ፍቅር ከልዩነት በኋላ ምክክር የሚለው ነው። ከልዩነት በፊት ፍቅር ልዩነት እንዳይፈጠር የሚያደርግ ሲሆን ከልዩነት በኋላ ምክክር ደግሞ ተፈጥሮ የነበረን ልዩነት የምንመልስበት ጥበብ ነው።

ኢትዮጵያ ቡራቡሬ ናት..ዥንጉርጉር። ይሄ ውበቷ..ይሄ ማማሯ ደግሞ እኔና እናት ነን። የእኔና የእናት የተለያየ መሆን ነው የተለየች ያደረጋት። ልዩነትን ለበጎ ነገር መጠቀም ጸጋና በረከት የሚያስገኝ የእድሎች ሁሉ እድል ነው። ባለን ብዝሃነትና የባህል ስብጥር መለያየትን ትተን በአንድ ብንቆም ብዙ የምናተርፈው ይኖር ነበር። ብዝሃነት የእድል መገኛ ነው። እድሉ የሚወጣው ደግሞ ፍቅርን አስቀድመን ስንከተል ነው።

ድሮና አሁንን ለአፍታ ጨረፍ ብናደርገው ብዙ ልዩነቶችን እናገኛለን። ፍቅር ያልገባበትን ዘመናዊነት ዓለም አታውቀውም። አራዳነታችንና ሥልጣኔአችን ፍቅርን ሳንይዝ በብቻ ጉዞ ያደረግን ብዙ ነን። እንዲህ አይነቱ አካሄድ ሀገር፣ ባህል፣ ታሪክ ይነጥቃል እንጂ ማንነት አያቆይም። ኢትዮጵያዊነት ደግሞ ብዙ እጆች በብዙ ሃሳብና በብዙ ጥበብ አላቁጠው ያጸኗት የእኔ የአንተ ያንቺና የሁላችን መልክ ናት። እናም ፍቅርና እርቅ የአዲሱ ትውልድ አዲስ አስተሳሰቦች ይሁኑ የመጨረሻ መልዕክቴ ነው።

# አረጋውያን የታወሱበት ማዕከል

**በኃይሉ አበራ**



የ80 ዓመት የእድሜ ባለጸጋዋ ወይዘሮ ዓይናለም ደሳለኝ በብዙ የሕይወት ውጣ ውረዶች ውስጥ አልፈዋል። በባለቤታቸው፣ በልጆቻቸው እንዲሁም በእናትና አባት ሞት ብዙ መጎዳታቸውን ይገልፃሉ።

“በልጅነት ካገኘኋቸው ሁለት ወንድ ልጆቼ ጋር ረሃብ ሲገርፈኝ የማበላቸው ሳጣ፤ አቅም ባለኝ ጊዜም ሰው ቤት እንጀራ እየጋገርኩ፣ ልብስ እያጠብኩ እየሠራሁ ማታ ያገኘኋትን አጎርሻቸዋለሁ።›› ሲሉ ያን የመከራ ዘመን የሚያስታወሱት ወይዘሮ አይናለም፤ ያለ አባት ያሳደጓቸው ልጆቻቸው አድገው ሰው ይሆናሉ ሲሉ በሞት መነጠቃቸውን ይገልጻሉ፡፡ በዚህ ሁሉ ተደራራቢ ኀዘን መጎዳታቸውን ጠቅሰው፣ ይህ ፈተናና አደጋ ለኀዘንና ብስጭት ብቻ ዳርጎ አልተዋቸውም፡፡ ተስፋ አስቆርጦ ጎዳና እስከመውጣት አድርሷቸዋል፡፡

በዚህ ሁሉ ማጥ ውስጥ ያለፉት ወይዘሮ አይናለም የሰንሻይን ፊላንትሮፊ የአረጋውያን መጠለያ እና መጦሪያ ማዕከል ስቦ እንዳወጣቸው ይናገራሉ፡፡ “ፈጣሪም በቃሽ ብሎኝ አሁን እዚህ ገብቼ ሌሊት እና ቀን ዓለም እያየሁ ነው። ስታመም ህክምና እያገኘሁ ምንም ሳይጎልብኝ እየኖርኩ ነው” ሲሉም ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ናቸው።

ማዕከሉ በቅርቡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ የተመረቀ ሲሆን፣ የተገነባውም በሰንሻይን ፊላንትሮፊ የአረጋውያን ፋውንዴሽን መስራችና ፕሬዚዳንት የክብር ዶክተር ሳሙኤል ታፈሰ ነው፡፡ ከከተማ አስተዳደሩ በሰሚት ኮንደሚኒየም አካባቢ በተሰጠው 30 ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ከ634 ሚሊዮን ብር በሚበልጥ ወጪ የተገነባው ይህ የአረጋውያን መጦሪያ ማዕከል በቅርቡ ነው ሥራ የጀመረው።

ወይዘሮ አይናለም አሁን በማእከሉ ችግራቸው ተፈትቷል፤ ስለሚበሉት፣ ጎናቸውን ስለሚያሳርፉበት ማሰብ አቁመዋል፡፡ ለህመማቸውም ህክምና እያገኙ በደስታ መኖር ጀምረዋል፡፡ የማእከሉ አገልግሎት የቀደሙትን ችግሮቻቸውን ሁሉ ረስተው በደስታ እንዲኖሩ እያረጋቸው መሆኑን ወይዘሮ አይናለም ይናገራሉ።

ከፈጣሪ በመቀጠል ይሄንን የመሰለ የአረጋውያን መጦሪያ አሳምረው ሠርተው ለአገልግሎት ላበቁትና እነሱን አሰባስበው ወደ ማእከሉ ላስገቡት ሁሉ ምስጋና አቅርበዋል። አንድ ቤት የሚቆመው ምሰሶ ሲኖረው ነው ያሉት ወይዘሮ አይናለም፣ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በመረዳዳት እና በመደጋገፍ መኖር እንደሚገባቸውም ነው የመከሩት።

የኮልፌ አካባቢ ነዋሪ የነበሩትና በወትድርና ለበርካታ ዓመታት ማገልገላቸውን የገለጹት አስር አለቃ አሰፋ በየነ የማእከሉ ተጠቃሚ ከሆኑት መካከል አንዱ ናቸው፡፡ አስር አለቃ አሰፋ በአዛውንት እድሜያቸው ብዙ ፈተናዎችን አሳልፈዋል፤ የሰው እጅ አይተዋል፡፡

በ19 ዓመታቸው ነበር የውትድርናውን ሕይወት የተቀላቀሉት፡፡ ኤርትራ ውስጥ ለ15 ዓመታት በውትድርና አገልግለዋል። ከአራት ጊዜ በላይ የመቁሰል አደጋ እንደደረሰባቸው የሚናገሩት አስር አለቃ አሰፋ፣ በ1981 ዓ.ም ከረን ላይ ከቆሰሉ በኋላ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ መደረጉን ይገልጻሉ። በ1982 ዓ.ም በ85 ብር “ቦርድ ወጣሁ” የሚሉት አስር አለቃ አሰፋ፣ በአዲስ አበባ ለጋብቻ ዝግጅት ላይ እያሉ በ“ዳግም ዘማች አባት ጦር” ጥሪ ተደርጎላቸው በጉደር ጥይት ፋብሪካ በቃኚነት እንደገና ሥራ መጀመራቸውን ያስታውሳሉ።

በ1983 ኢህአዴግ አዲስ አበባ ሲገባ ደግሞ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ፡፡ በወቅቱ ሠራዊቱ ሲበተን ጡረታቸውን ለማስከበር ብዙ እንግልት ደርሶባቸዋል፡፡ ጉዳዩ እስከፈጸም በሚል በአናጢነት ሲሰሩ ቆይተው የ85 ብር ጡረታ ተከፋይ ይሆናሉ፡፡ ሀገር ሰላም ነው ብለው ሶስት ልጆቻቸውንም ሰብስበው መኖር ይጀምራሉ፡፡

አሁንም የቀድሞ ሠራዊት በሚል ማሳደድ የደረሰባቸው እኚህ የሀገር ባለውለታ፣ “የደርግ አባል ነህ” መባላቸውን ይናገራሉ፤ እሳቸው ደግሞ የኢትዮጵያ ሠራዊት ነኝ የሚል ምላሽ ይሰጣሉ። ቀጣይ እጣ ፈንታቸው በእስር ጦላይ መወሰድ ሆነ። በዚያም ምርመራ ሲደረግላቸው ምንም የተመዘገበ ወንጀል ስላልተገኘባቸው ይለቀቃሉ።

በተደጋጋሚ ጊዜ የደርግ አባል በሚል ያለምንም ምርመራ ታስረው እንደነበር የሚያስታወሱት አስር አለቃ አሰፋ፣ በደረሰባቸው እንግልት ተስፋ በመቁረጥ ገጠር ገብተው ከብት ጠባቂ ሆኑ። ያም አልሆን ሲላቸው አዲስ አበባ የተመለሱት አስር አለቃ አሰፋ፣ በየቤተክርስቲያኑ ደጅ በመቆም እስከመለመን ደርሰዋል፡፡ ቃሊቲ መናኸሪያ አካባቢ ባለው አረጋውያን መጠለያ ለዘጠኝ ዓመታት ኖረዋል።

‹‹ወደዚህ ዓለም ወደ ሆነው የአረጋውያን መጠለያ በመግባቴ ደስታዬ የላቀ ነው›› የሚሉት እኚህ የሀገር ባለውለታ፣ በማእከሉ አገልግሎት በእጅጉ መርካታቸውን ይገልጻሉ፡፡ አግልግሎቱን ሲያስቡት “ይቺ ሀገር አለች ወይ›› በማለት ራሳቸውን እንዲጠይቁ እያረጋቸው መሆኑን ነው በአድናቆት የሚናገሩት፡፡



**ወይዘሮ ዓይናለም ደሳለኝ**



**ወይዘሮ ፈቃደነሽ ዳንኤል**

“ጠይቆን፣ ተንከባክቦን፣ በምግብም፣ በመኝታም ይሄንን የመሰለ ምቾት በእድሜዬ አላየሁም” ሲሉም የድርጅቱን መስራች አመስግነው፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቀው የቀድሞ የኢትዮጵያ ሠራዊት መበተኑ የብዙዎችን ሞራል ክፉኛ መጉዳቱን ተናግረዋል፡፡ እሳቸውም የዚህ ሰለባ መሆናቸውን ገልጸው፣ መንግሥት ከዚህ በመማር እያደረገ ያለውን መሻሻል አድንቀዋል። በሀገራችን ሰላም ጉዳይ ላይ መንግሥት ጠንክሮ ሊሠራበት ይገባል ብለዋል፡፡

ማእከሉ በተመረቀበት ወቅት እንደተገለጸው፤ ማእከሉ 750 አረጋውያንን የመቀበል አቅም አለው፡፡ የራሱ ክሊኒክ፣ የመድሃኒት መደብር፣ የመጻህፍት ቤት፣ ላውንደሪ፣ መመገቢያ አደራሽና መዝናኛ ክበቦችም አሉት፡፡ በአጠቃላይ ለአረጋውያን ምቹ ተደርጎ የተገነባ ነው፡፡

የማዕከሉ ጊቢ አረንጓዴ እና ለእይታ ማራኪ መናፈሻ ቦታዎች በስፋት ያሉት ይህ ማእከል፣ ለአረጋውያኑም የጤና፣ የምግብ የአልባሳት እንዲሁም የተለያዩ የዕደ ጥበባት ማዕከሎች የተሟሉለት ነው።

የሰንሻይን ፊላንትሮፊ ፋውንዴሽን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሳምሶን ተስፋዬ እንደገለጹት፤ ፕሮግራሙ ዘለቄታዊነት እንዲኖረውም የተገነባው ተጨማሪ ባለሁለት ወለል የገበያ ማዕከል ህንጻ የኪራይ ገቢ ለ750 አረጋውያን የምግብ፣ የጤና፣ የንጽህና እና ሌሎች ግበዓቶችን ማሟላት ያስችላል። ከፍተኛ የወንድ አረጋውያን ወደጎዳና የሚወጡ መሆኑ በጥናት በመለየቱም 500 ወንዶች እና 250 ሴት አረጋውያንን ይይዛል። የአረጋውያን ማዕከሉ ዝቅተኛ ወርሃዊ ወጪ አራት ሚሊዮን ብር ያህል መሆኑንም አቶ ሳምሶን ጠቁመዋል።

አረጋውያኑም ኮሚቴ አቋቁመው እርስበርሳቸው የሚደጋገፉበት እና የሚመካከሩበት ሁኔታ የተመቻቸ ሲሆን፣ ቀለል ያሉ የሻማ፣ የጧፍ፣ የነጠላ፣ የጋቢ፣ ሥራዎችንም ሠርተው ገቢ የሚያገኙባቸው ማዕከላት ተዘጋጅተዋል።

ፕሮጀክቱን በጋራ የሚደግፉ ባለድርሻ አካላትም ከአዲስ አበባ ከተማ ሴቶችና ህፃናት እና አረጋውያን ቢሮ ጋር በመፈራረም ጧሪ ደጋፊ የሌላቸውን አረጋውያን እየመለመሉ በጋራ እየሠሩ ናቸው። እክል ሲያጋጥም በማዕከሉ በተደራጀ አንደኛ ደረጃ የህክምና ማዕከል የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እንዲያገኙ ይደረጋል። በማዕከሉ መደገፍ የማይችሉም ከወረዳው ጤና ቢሮ ጋር ትስስር ይደረጋል። የከፋ ከሆነም ከየካቲት 12 ሆስፒታል ጋር በመተደረገ ትስሰር መሠረት ክትትል እንደሚደረግላቸው ዋና ሥራ አስኪያጁ አመላክተዋል።

አረጋውያንን የሚጦሩ፣ ህፃናት ልጆችን የሚደግፉ፣ በርካታ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ቢኖሩም፣ ቀጣይነት ያለው ድጋፍን ለማከናወን ቋሚ ገቢ ማግኘት ላይ ይቸገራሉ ያሉት ዋና ስራ አስኪያጁ፣ ከገበያ ማዕከሉ የሚገኘው ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የኪራይ ገቢ ተሰብስቦ በቀጥታ ለአረጋውያን መጦሪያ ማዕከሉ መተዳደሪያ እንደሚውልም አስታውቀዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአረጋውያን መጦሪያ እና መንከባከቢያ የሰንሻይን ፊላንትሮፊ ፋውንዴሽን ፕሮግራም ኦፊሰር እና ካውንስለር ወይዘሮ ፈቃደነሽ ዳንኤል በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ማዕከሉ በአሁኑ ወቅት 54 ወንዶች እና 17 ሴቶች በጠቅላላው 71 ጧሪ ቀባሪ የሌላቸው አረጋውያንን ተቀብሎ ከጳጉሜ አንድ 2016 ጀምሮ አገልግሎቱን እየተሰጠ ይገኛል።

ማዕከሉ የህክምና፣ የምግብ፣ መጠለያ እና አልባሳት እንዲሁም የሥነልቦና ድጋፍ ይደረግላቸዋል ያሉት ወይዘሮ ፈቃደነሽ፣ አሁን ላይ ሙሉ በሙሉ ወጪውን የሰንሻይን ኮንስትራክሽን እየሸፈነ ሲሆን፣ በቀጣይ ግን በማዕከሉ የተገነባው ሞል ተከራይቶ የሚገኘው ገቢ ሙሉ በሙሉ ለማዕከሉ መተዳደሪያ እንደሚውል ገልጸዋል። በማዕከሉ የሚሰሩ ለ150 ሠራተኞችም ቋሚ የሥራ ዕድልም ተፈጥሮላቸዋል ብለዋል።

ማእከሉን የመረቁት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው፣ ማዕከሉ አረጋውያን ጉልበት ባላቸው እና በጉበዝና ዘመናቸው ሃላፊነትን ተወጥተው ትውልድን ቀርፀው ሀገርን ያገለገሉ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በመጨረሻው እድሜያቸው የተጣሉ እና የወደቁ እንዳይሆኑ፣ ለምድራቸው በረከትን ትተው እንዲሄዱና እንዳይማረሩ የሚያደርጉ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

ይህ ማዕከልም በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል እና አረጋውያኑ ሥራ ጭምር እንዲሠሩ የሚያስችላቸው በርካታ ለአገልግሎት ምቹ የሆኑ መሠረተ ልማቶች የተገነቡለት መሆኑንም አስታውቀዋል። መንግሥት ብቻ ሰርቶ የዜጎችን ጥያቄ መመለስ፣ የዜጎችን ጫና መቀነስ ሕይወትን መመለስ እንደማይቻል በመረዳት በልብ ቀናነት የሚከናወኑ መሰል የማህበራዊ ኃላፊነት ሥራዎች በመዲናዋ ባህል እየሆኑ መምጣታቸውንም ከንቲባዋ ተናግረዋል። የከተማዋ ባለሀብቶች ቢዝነስ ሠርተው ማትረፍ ብቻ ሳይሆን ሰው ተኮር የልማት ሥራዎችን ሰርተው የዜጎችን የኑሮ ጫና እንዲያቃልሉ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ተገቢ መሆኑን አመላከተዋል።

የማእከሉ መስራች አቶ ሳሙኤል ታፈሰ የተለያዩ ኢንቨስትመንቶች ባለቤት ናቸው፡፡ እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አነስተኛ የገቢ ምንጭ ካለው ቤተሰብ የተገኙ መሆናቸውን ከድርጅቱ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። የስምንተኛ ክፍል ተማሪ በነበሩበት ወቅትም የትምህርት ቤት ክፍያ ለመክፈል ተቸግረው እንደነበር መረጃው አስታውሶ፣ ይህን ችግር ለማሸነፍ ለስላሳ በመሸጥ እና ሌሎች ሥራዎችን በመሥራት ራሳቸውን ያስተማሩ መሆናቸውን ጠቁማል።

አቶ ሳሙኤል የትምህርት ቁጭታቸውን ለመወጣት በገቢ እጥረት ሳቢያ ወደ ትምህርት ቤት ሳይሄዱ የሚቀሩ ተማሪዎችን ለማገዝ ከራሳቸው ተሞክሮ በመውሰድ ትምህርት ቤቶችን ከፍተው ተማሪዎችን እየረዱ ይገኛሉ። በዚህም ሀገራዊ የበጎ ሥራዎችንና እና ማህበራዊ ኃላፊነቶቹን ለመወጣትም የትምህርት እድል ማግኘት በሚገባቸው እድሜ ጎዳና ወጥተው የሊስትሮ፣ የናብኪን ሽያጭ እና መሰል ሥራዎችን እየሠሩ የሚገኙ ልጆችን በመሰብሰብ በሀገሪቱ የተለያዩ ክልሎች የትምህርት እድል እንዲያገኙ አድርገዋል።

በመሆኑም በትግራይ አክሱም፣ በኦሮሚያ ነቀምት፣ በደቡብ አገና እንዲሁም በአማራ ደብረብርሃን ከተማ ላይ ትምህርት ቤቶችን በመገንባት፣ የተማሪዎችን ሙሉ ወጪ በመሸፈን እና የኪስ ገንዘብ 250 ብር በመክፈል በርካታ ተማሪዎችን ላለፉት 12 ዓመታት እየደገፉ ይገኛል። አቶ ሳሙኤል የትምህርት ቤቶቹን መተዳደሪያ ወጪ በቋሚነት ለማግኘትም ፊላሚንጎ አካባቢ ያለውን ባለ 12 ወለል ህንጻ በማከራየት ትምህርት ቤቶቹ እንዲተዳደሩበት አድርገዋል።

አሁን ለአረጋውያን የቋቋመው ማእከል የአቶ ሳሙኤል ማህበራዊ ሃላፊነትን የመወጣት ሁለተኛው ምእራፍ መሆኑም ተገልጿል፡፡ በዚህ ምዕራፍ የማህበራዊ ሃላፊነት ሥራቸውን ለሀገራቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሲያደርጉ፣ ወገን ሲረዱ ሀኪም ሆነው ያገለገሉ እና በማምሻ እድሜያቸው ላይ የሚጦራቸውና የሚደግፋቸውን ያጡ እና ቤተክርስቲያን እና መስጊድ አካባቢ ድጋፍ በመጠየቅ ሕይወታቸውን ሲመሩ የነበሩ አረጋውያንን መርዳት እና መደገፍ ሥራውን ጀምሯል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# ከወዳደቀ ብረታብረት ተሽከርካሪ የሠራው ወጣት

ክብረአብ በላቸው

ቴክኖሎጂና አዲስ የፈጠራ ሥራ የሰው ልጆችን ሕይወት በብዙ አሻሽሏል። ከትምህርት ከጤና፣ ከግብርና እና ከሌሎች ዘርፎች አንፃርም የሚሰጠውን ጠቀሜታና የአጠቃቀም ሂደቱን ብንመለከት እንደ ዘርፎቹ ዓይነት ጥቅም ላይ የሚውልበት መንገድም ይለያያል። የሚጠቀምባቸው መሳሪያዎችም እንዲሁ እንደ አገልግሎቱ ዓይነትና ስፋት ይለያያሉ።

እንደ ኢትዮጵያ ላሉና በማደግ ላይ ለሚገኙ ሀገራት ደግሞ የቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራ ፋይዳው ከምንለው በላይ ትልቅ ነው። በተለያዩ ዘርፎች ላይ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የማደግ ዕድል እንዳላት ሀገር፣ የማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ ለመሻሻል፣ ለትምህርት ለግብርና ለጤና ለወታደራዊ አገልግሎት፣ በአጠቃላይ በሁሉም ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን በቴክኖሎጂና በአዳዲስ የፈጠራ ሥራ መታገዝ የግድ ሆኗል፤ ያለ ቴክኖሎጂ ያለሙበት መድረስ የማይታሰብ ከሆነ ሰነባብቷል።

ወጣት ታምራየሁ አየለ ይበላል፤ ትውልድና ዕድገቱ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሀዲያ ዞን በምትገኝ ሞርሱጦ በተባለች አነስተኛ የገጠር ከተማ ነው። በአሁኑ ወቅት ደግሞ ነዋሪነቱ በዞኑ መዲና ሆሳዕና ከተማ ውስጥ ነው። ወጣቱ ገና ከመነሻው ጀምሮ ለፈጠራና ለቴክኖሎጂ ነክ ሥራዎች ዝንባሌ የነበረው ሲሆን ይህም ተሰጦ አድጎ ተስፋ ሰጪ የሆነ የፈጠራ ሥራ እንዲያበረክት አብቆቶታል።

ወጣት ታምራየሁ በከተማው "ታሜ የብረታብረት ሥራ" በተባለ ድርጅት ላለፉት ጊዜያት እየሰራ የቆየ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በዙሪያው የሚያገኛቸውን የወዳደቁ ብረታ ብረቶችን በመጠጋገን አነስተኛ መጠን ያላትን ተሽከርካሪ መሥራት ችሏል።

ከልጅነቱ ጀምሮ የፈጠራ ሥራዎችን ይሰራ እንደነበር የሚናገረው ወጣት ታምራየው ፤ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ በነበረበት ወቅት ማለትም የሰባት እና የስምንት ዓመት ሕፃን ሳለ በሽቦ መልክ የተሰሩ መኪኖችን በራሱ ሰርቶ በጨዋታ መልክ ይገለገልባቸው እንደነበር ትውስታውን ይናገራል።

ለቴክኖሎጂና ለአዲስ የፈጠራ ሥራ ያለው ፍላጎት የጀመረው በመኖሪያ አካባቢያቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ዝርጋታ በሚከናወንበት ወቅት እንደነበር የሚናገረው ወጣት ታምራየሁ፤ ከባለሙያዎቹ ጋር በልጅነት ዕድሜ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ማለትም ውሃ፣ መፍቻና መሰል ነገሮችን በመላላክ እያቀረበ ወዳጅነት ፈጠረ። ይህ ነገርም ቀልቡን ስለገዛው ወደ ፈጠራ ሥራ ተሳበ።

በወቅቱ የ12ዓመት ታደጊ የነበረው ታምራየሁ በትውልድ አካባቢው የመብራት መሠረተ ልማት ከተዳረሰ በኋላ እርሱ ቀደም ሲል አብሮ በመዋል፤ የሚያወሩትን ነገር በመስማት፤ ያልገባውን ነገር ደግሞ በመጠየቅ በርካታ ዕውቀቶችን ጨብጧል። ባገኘው እውቀትም በወቅቱ በአካባቢያቸው የኤሌክትሪክ ባለሙያ ዕጥረት ስለነበር በአካባቢው ከቤት ቤት ኤሌክትሪክ በመዘርጋት ገቢውን ማሳደግ ችሏል።

ወጣት ታምራየሁ የልጅነት ጊዜውን ወደኋላ መለስ ብሎ አስታውሶ ሲናገር፤ ቤተሰቦቹ ከኤሌክትሪክ ጋር ያለው መቀራረብ ስላልወዳዱት በተደጋጋሚ ሥራውን እንዲያቆም ቢነግሩትም እርሱ ሊያቆም ባለመቻሉና የቤተሰብን ማስጠንቀቂያ ችላ በማለቱ ለግርፋት ተደርጎ እንደነበር ይናገራል። በኋላ ላይ ግን ኤሌክትሪክ በጥንቃቄ ከተሰራ የማይጎዳ መሆኑን በማስረዳትና ቤተሰቡም ሁኔታውን በመገንዘቡ ሥራውን ስለመቀጠሉ ይናገራል።

ወጣቱ እንደሚናገረው፤ ለአዳዲስ ፈጠራዎች ሁልጊዜ ጉጉ በመሆኑ የ8ኛ ክፍል ተማሪ በነበረበት ወቅት ከወላጅ አባቱ ጋር ከመኖሪያ አካባቢው ወጣ ብለ ወዳለች ከተማ በሄደበት ወቅት ባለሶስት እግር ተሽከርካሪ ባጃጅ እንደተመለከተ ይናገራል። በወቅቱ ለወላጅ አባቱ ``አባቴ ይህንን ባጃጅ እኔ መሥራት እፈልጋለሁ'' የሚል ሃሳብ ይሰነዝራል።

ወላጅ አባቱም ‹‹እንዴት አድርገህ ነው የምትሰራው ?›› የሚል ጥያቄ ያቀርቡለታል።`` ቤት ውስጥ ያለውን የአሮጌ ሬዲዮ በመፍታት እንዲጠቀም ከፈቀድክልኝ አንቀሳቅሼ ማሳየት እችላለሁ'' በማለት ከወላጅ አባቱ ባገኘው መልካም ምላሽ ወደ ሥራው እንደገባ ይገልፃል።

ከሬዲዮ ዲናሞ በማውጣት ዲናሞ ነክ ነገሮች negative ከpositive ጋር ሲሆን ወደፊት positive ከnegative ጋር ሲሆን ደግሞ ወደ ኋላ የመሽከርከር ባህርይ ስላላቸው እርሱን በመጠቀም ከችንጋ ጋር በማገናኘት የኋላና የፊት ማርሽ በማድረግ መሥራት እንደቻለ ወጣት ታምራየሁ ያስታውሳል።

ወጣት ታምራየሁ እንደሚናገረው፤ ወላጅ አባቱ ልጃቸው በልጅነቱ በሠራው የፈጠራ ሥራ ከፍተኛ ደስታ ስለተሰማቸው ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ ሙያውን መለማመድ እንዲችል በማሰብ ከአካባቢው ብዙዎች ወደሚሄዱበት ደቡብ አፍሪካ እንደላኩት ይናገራል። ወጣቱ እንደሚገልፀው፤ የእርሱን የውጭ ጉዞ ከሌሎች የአካባቢው ወጣቶች ለየት የሚያደርገው የፈጠራ ሥራውን ክህሎት ወደ ውጭ ሀገር በመሄድ ማዳበር እንዲችል ተስቦ የመጣ መሆኑ ይናገራል።

በደቡብ አፍሪካ ቆይታው ከሌሎች የሀገሩ ወጣቶች በተለየ መልኩ በተለያዩ የመኪና ጋራዦች ውስጥ ተቀጥሮ በመሥራት ሙያውን ለማሳደግ ጥረት ስለማድረጉ የሚናገረው ወጣት ታምራየሁ፤ በመጀመሪያ አካባቢ እንደውም ያለ ደመወዝ ክህሎቱን ከፍ ለማድረግ ባለው ፍላጎት ብቻ ለረዥም ጊዜ ሲሰራ እንደቆየ ይገልጻል።

ታምራየሁ እንደሚለው ፤ በደቡብ አፍሪካ ቆይታው ከአንድ የሀገሩ ልጅ ጋር በመሆን በተለያዩ ጋራዦች ጥቂት ገንዘብ እየተከፈላቸው ሲሰሩ በቆዩበት ጊዜ በቀሰሙት እውቀት የራሳቸውን ጋራዥ በመክፈት በግጭትና በተለያዩ ጉዳቶች አገልግሎት የማይሰጡ መኪኖች በኢንሹራንስ በኩል በጨረታ ስለሚሸጡ እነኚህን መኪኖች በጨረታ በመግዛት ወደ እነርሱ ጋራዥ በመውሰድ፤ በመጠገንና በማስጠገን መኪኖችን ለኢትዮጵያውያን የመሸጥ ሥራ ሲሰራ እንደነበር ይናገራል።

ከደቡብ አፍሪካ ወደ ሀገር ውስጥ በመመለስ በስደት እያሉ ባካበቱት እውቀት ከጓደኛው ጋር በመሆን "ታሜ የብረታብረት ሥራ" የተባለ ድርጅት በመቋቋም የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎች የታከሉበት ሥራ ሲሰሩ እንደቆዩ የሚናገረው ወጣት ታምራየሁ፤ የተለያዩ ነገሮችን ሲያከናውን ባገኘው ክህሎት ከወዳደቁ ብረታብረቶች አነስተኛ መኪና መሥራት ስለመቻሉ ያስረዳል።

ይህንን ሥራ ለመሥራት ምን እንዳነሳሳው ወጣቱ ሲናገር፤ ‹‹ኢትዮጵያ ከሸማችነት ወደ አምራችነት በምታደርገው ጉዞ ላይ የበኩላችንን አስተዋጽኦ ማበርከት አለብን በሚል እና ተሽከርካሪዎች ከውጭ ሲመጡ ከቀረጥና ታክስ ጋር ተያይዞ ያለውን የዋጋ ንረት ከግንዛቤ በማስገባት ይህንን ሥራ ለመሥራት ተነሳስቻለሁ። በዋነኝነት ደግሞ ኢትዮጵያ ካላት አነስተኛ የውጭ ምንዛሬ አንፃር ለመኪና ግዥ የምትወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ለማስቀረት በማለም ወደ መኪና ማምረት ላይ ትኩረቴን አድርጌለሁ››ሲል ይገልፃል።

ሌላኛው ጉዳይ በዘርፉ የተማረ የሰው ኃይል የሥራ ዕድል እንዲያገኝ በማሰብ ወደዚህ ሥራ እንደገባ የሚናገረው ወጣት ታምራየሁ፤ ገና ከጅምር ባለው ሥራ ለወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጥሮ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማሰብ ሥራውን አጠናክሮ ስለመቀጠሉ ያስረዳል።

ወደፊት የኤሌክትሪክ ቻርጅ እንጅኖችን ከውጭ ሀገር በማስመጣት ኢትዮጵያ በኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ያላትን ምቹ አጋጣሚ በመጠቀም ሀገሪቱ ለነዳጅ ግዥ የምታወጣውን ከፍተኛ ገንዘብ ለመቀነስ ዕቅድ እንዳለው የሚናገረው የፈጠራ ባለሙያው ወጣት ታምራየሁ፤ የሻንሲና የተቀሩ የመኪና ክፍሎችን እዚሁ በመገጣጠም ለማህበረሰቡ መኪና ተደራሽ ለማድረግ ጥረት እያደረገ ስለመሆኑ ገልጿል።

1300 ሲሲ የፈረስ ጉልበት ስላላትና በእርሱ እጅ ስለተሰራችው ተሽከርካሪ ወጣቱ ሲናገር፤‹‹ ከ50ና 60 ዓመት በላይ አገልገሎት ሰጥተው ከተጣሉ ተሽከርካሪዎች ብረት በመሰብሰብ ሻንሲውን ደግሞ ሙሉ በሙሉ እንደገና ዲዛይን በማድረግ የመንገድና የአካባቢውን መልከዓ ምድር ታሳቢ ባደረገ መልኩ ለመሥራት ሞክሬአለሁ። የመኪናውን የቦዲ ክፍል ደግሞ በሃይድሮሊክ ተገፍቶ በማሽን አማካኝነት እንጂ በሰው እጅ መምጣት የሚከብዱ ከርቮችን በመሥራት ዕውን ማድረግ ችያለሁ። በተጨማሪም የኤሌክትሪክ ዲዛይኑን ሙሉ እንዲሁ የወደፊት የድርጅታችንን ምርቶች ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንዲሰራ አድርጌለሁ።›› ብሏል።

የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ሳይንስና ቴክኖሎጂ ቢሮ እስከ መሥሪያ ቤታቸው ድረስ በመምጣት ድጋፍና ክትትል በማድረግ ለተሰሩ ሥራዎችም የምስክር ወረቀቶች የድጋፍ ደብዳቤ በመስጠት እንዳበረታቱት የተናገረው ወጣት ታምራየሁ፤ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ፣ የዞኑና የክልሉ መንግሥት ለሥራው አጋርነት በማሳየት ድጋፋቸውን በማድረግ ላይ እንደሚገኙ ጠቁሟል።

ወደፊት በዘርፉ ውጤታማ ለመሆን የረዥምና የአጭር ጊዜ እቅዶችን በመውጣት እየሰራ እንደሆነ የሚናገረው ወጣቱ፤ በረዥም ጊዜ የሞተር ክፍሎችን ከውጭ በማስመጣት የተሽከርካሪ ማምረቻ ለመክፈትና አቅም ማጎልበት ሲቻል ደግሞ ሙሉ በሙሉ ሀገር ውስጥ መኪና የማምረት ግብ አስቀምጦ እየሰራ መሆኑን ገልጿል።

ወደዚያ ደረጃ ለመሸጋገርም ባለው ጊዜ ውስጥ የከተማ ቆሻሻ ማስወገጃ ማሽን፣ በግብርና ዘርፍ ደግሞ የእርሻ ትራክተር ለገበሬዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ለማድረስ እየሰራ እንደሆነ እና በአሁኑ ወቅትም ምንም ዓይነት አቧራ በሌለው መልኩ የከተማ ቆሻሻ ማስወገድ የሚችል መኪና ሰርቶ በመጠናቀቅ ለሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ለማስረከብ በዝግጅት ላይ እንዳለ ተነግሯል።

መንግሥት በየአካባቢው እንደ እርሱ ዓይነት የፈጠራ ዝንባሌ ያላቸው ወጣቶች ሥራቸውን ማጎልበትና ማሳደግ የሚችሉባቸውን የፈጠራና የቴክኖሎጂ ማዕከላት ቢኖሩ የተሻለ ሥራ መሥራት እንደሚቻል እና የቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራ በይበልጥ ድጋፍና ክትትል የሚያገኙበት መንገድ ቢኖር መልካም ነው ይላል።


የልጅነት ህልሙን ለመኖርና ሥራውን ለመሥራት ጥረት በሚያደርግበት ወቅት ከሚያጋጥሙት ተግዳሮቶች አንዱ ከአንዳንድ ግለሰቦች የሚሰጥ አሉታዊ አስተያየት ነው። በተለይም ‹‹መኪና ኢትዮጵያ ውስጥ መሥራት የማይታሰብ ነው አንተ መኪና እሰራለሁ ብለህ አትልፋ›› የሚሉ አሉታዊ አስተያየቶችም ይደርሱት ነበር። እርሱ ግን ያንን ፋይዳ አልባ አስተያየት ለመስማት ጆሮ እንዳልሰጠ ይናገራል።

አሁን ያለንበት ዘመን ሁሉንም ነገር በቀላሉ በእጃችን ማግኘት የምንችልበት የቴክኖሎጂ ዘመን ነው የሚለው ወጣት ታምራየሁ የማይቻል ነገር የለም ይላል።

‹‹ገንዘብ የለኝም፤ የሚያግዘኝ ሰው የለም'' በማለት የተቀመጡ ወጣቶች አሉ። ይህ መሆን የለበትም። የተወሰነ ዕውቀት ካለ ያንን በማዳበር ባላቸው ግብዓት ብቻ ከቀላል ነገር በመጀመር ለመሥራት ዝግጁ መሆን አለባቸው።›› የሚል ምክሩን ይለግሳል።

ሕልምን ለማሳካት ሁልጊዜም ዋጋ መክፈል ይኖራል የሚለው ወጣቱ፤ ጠንክረው ከሰሩ ከሳቡበት መድረስና ያለሙትን ግብ ማሳካት እንደሚቻል ይናገራል። ስለዚህ ``ኢትዮጵያን አንድ ደረጃ ላይ የማድረስ ግዴታና ኃላፊነት እስካለብን ድረስ'' ወጣቶች ለዓላማቸው መሳካት መክፈል ያለባቸውን መስዋዕትነት ሁሉ መክፈል እንዳለባቸው ተሞክሮውን በመጥቀስ ያስረዳል።

በተለይም ለአሉታዊ አመለካከቶች ቦታ ባለመስጠት ፤ የነገው ራዕያቸውን ከግብ ለማድረስ ቀን እና ሌሊት ተስፋ ሳይቆርጡ መትጋት እንደሚኖርባቸው ምክሩን ይለግሳል። ጠልፈው ለመጣል ከፊት የሚቀድሙ መሰናክሎች ቢኖሩም ነገን አሻግሮ መመልከት እንዳለባቸው መልዕክቱን ያስተላልፋል።




**የልጅነት ህልሙን ለመኖርና ሥራውን ለመሥራት ጥረት በሚያደርግበት ወቅት ከሚያጋጥሙት ተግዳሮቶች አንዱ ከአንዳንድ ግለሰቦች የሚሰጥ አሉታዊ አስተያየት ነው። በተለይም «መኪና ኢትዮጵያ ውስጥ መሥራት የማይታሰብ ነው አንተ መኪና እሰራለሁ ብለህ አትልፋ» የሚሉ አሉታዊ አስተያየቶችም ይደርሱት ነበር**

# እየተነቃቃ ያለው የእምነበረድ ማዕድን ልማት

**ወርቅነሽ ደምሰው**



የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በማዕድን ሀብት የታደለ ነው። ክልሉ በስፋት ከሚታወቅባቸው ማዕድናት መካከል ወርቅ አንዱ ነው። የወርቅ ማዕድኑ በባህላዊ መንገድ በማህበራት እየለማ ሲሆን፣ ምርቱም ለብሔራዊ ባንክ ገቢ እየተደረገ ለሀገር የውጭ ምንዛሬ እያስገኘ ነው፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ወርቅን በኩባንያ ለማምረት የሚያስችሉ ተግባሮች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

የማዕድን ልማቶቹ፣ በተለይ የወርቅ ማምረት ሥራው፣ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር እየቻሉ ነው። የወርቅን ያህል ባይሆንም የሌሎች ማዕድናት ልማት ተግባርም ለዜጎች የሥራ እድል መፍጠር ችለዋል።

የክልሉ ማዕድን ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ካሚል ሀመድ እንደሚገልጹት፤ በክልሉ እንደ ወርቅ ካሉት የከበሩ ማዕድናት በተጨማሪ ለኢንዱስትሪና ለግንባታ ግብዓትነት የሚውሉ ሌሎች በርካታ ማዕድናት በስፋት ይገኛሉ። ኮንስትራክሽን ግብዓት ማዕድናት መካከል ለግንባታ ማጠናቀቂያነት የሚውለው እምነበረድ አንዱ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ እንደ ሲሚንቶ ፋብሪካ ላሉ ኢንዱስትሪዎች የኃይል ምንጭ በመሆን እያገለገለ ያለው የድንጋይ ከሰል ነው።

ከእነዚህ በተጨማሪ በምርት ደረጃ የማይታወቁም ሌሎች በርካታ ማዕድናት በክልሉ አሉ የሚሉት ኃላፊው፤ ሌሎች በክልሉ አሉ የተባሉት ማዕድናት ላይ ጥናት እየተካሄደ መሆኑንም ተናግረዋል። በግኝት ያልተረጋገጡ የማዕድናት ዓይነቶች በርካታ መሆናቸውንም አስታውቀዋል።

ቀደም ሲል የእምነበረድ ማዕድን ልማት በስፋት ሲካሄድ እንደነበር ኃላፊው አስታውሰው፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ከጸጥታ ችግር ጋር በተያያዘ በሚፈለገው ልክ እየተመረተ እንዳልሆነ አስታውቀዋል። ዘንድሮ እምነ በረድ በማምረቱ ሂደት ከሌላው ጊዜ የተሻለ ውጤት እየተመዘገበ እንደሚገኝም ጠቁመዋል።

በተመሳሳይ በድንጋይ ከሰል ምርትም ካለፈው ዓመት የተሻለ ምርት እየተገኘ መሆኑ የተጠቆመ ሲሆን፣ ይህ ደግሞ ክልሉ በማዕድን ልማት ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ተመራጭ እንዲሆን የሚያደርጉ የኢንቬስትመንት አማራጮች እንዳሉት እንደሚጠቁም ተመልክቷል።

ዘንድሮ ለኮንስትራክሽን ሥራዎች በግብዓትነት የሚያገለግለውን እምነበረድ ማዕድን የማምረት ሥራ ተጠናክሮ መቀጠሉን ኃላፊው ጠቅሰው፣ ባለፉት ጊዜያት በክልሉ በታየው የጸጥታ ችግርና አለመረጋጋት ምክንያት እምነበረድ ለማምረት የሚያስችል ሁኔታ እንዳልነበር ገልጸዋል። ባለፈው ዓመት እምነበረድ የማምረት ሥራ አፈጻጸም በጣም ዝቅተኛ እንደነበርም አስታውሰዋል።

በበጀት ዓመቱ 20ሺ ሜትር ኪዩቢክ ለማምረት ታቅዶ 1ሺ.327ሜትር ኪዩቢክ እምነበረድ ብቻ መምረቱን ነው ኃላፊው ያመለከቱት። ከዓመት በፊት በክልሉ ከነበረው የጸጥታ ችግር ጋር ተያይዞ እምነ በረድ ለማምረት ፈቃድ ወስደው በዘርፉ የኢንቨስትመንት ሥራ የተሰማሩት ትልልቅ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ለማድረግ የማይችሉበት ሁኔታ እንደነበርም አስታውሰዋል። ችግሩ በዘርፉ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ እንዳይካሄድ ማድረጉን ነው ኃላፊው የተናገሩት።

ዘንድሮ በእምነበረድ ልማቱ የተሻሻለ አፈጻጸም ሊታይ እንደሚችል ኃላፊው ጠቅሰው፣ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት አፈጻጸም እየታየ ካለው አፈጻጸም መረዳት የሚቻለውም ይህንኑ መሆኑን ገልጸዋል። በ2016 በጀት ዓመት በሩብ ዓመት ውስጥ 2ሺ ሜትር ኪዩብ ለማምረት ታቅዶ፤ 209 ሜትር ኪዩብ እምነ በረድ ማምረት መቻሉን አስታውቀዋል። የመጀመሪያው ሩብ ዓመት አብዛኛው ወቅት ክረምት መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህ ሁኔታም ለማዕድን ልማት ምቹ እንዳልሆነ ተናግረዋል። ሩብ ዓመቱ ብዙ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ማድረግ የማይቻልበት ወቅት መሆኑን ገልጸው፣ የምርቱ መጠን ያነሰውም በዚህ ምክንያት መሆኑን ተናግረዋል። ከሁለተኛው ሩብ ዓመት ጀምሮ እምነበረድ በእጥፍ መመረት የሚቻልባቸው ሁኔታዎች እንዳሉም አመላክተዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ለማዕድን አምራቾች ፈቃድ የሚሰጠው በሁለት ዓይነት መንገድ ነው፤ በክልሉ እምነ በረድ በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ያሉ ሲሆን፣ አምራቾቹም ከፍተኛ ባለፈቃድ አምራቾችና አነስተኛ አምራቾች ተብለው ፈቃድ የወሰዱ ናቸው። ከፍተኛ ባለፈቃድ አምራቾች ፈቃድ የሚሰጣቸው በማዕድን ሚኒስቴር ነው። አነስተኛ አምራቾች የሚባሉት ደግሞ ከክልሉ ፈቃድ ወስደው በማምረት ሥራ ላይ ይሰማራሉ።

በክልሉ የእምነ በረድ ማዕድንን ለማምረት ከ200 በላይ ባለሀብቶች ፈቃድ ወስደው እየሰሩ ይገኛሉ። እነዚህ ባለሀብቶች ካምፖቻቸውን አድሰው ወደሥራ መግባት የሚችሉበትን ሁኔታ ለመለየት እየተሰራ ነው። አብዛኛዎቹ የመሥሪያ ቦታዎች በአምራቾች እጅ ሲሆኑ፣ ወደ ማምረት ሥራ መግባት ሲፈልጉ ካምፓቸውን አድሰው ሥራ መጀመር የሚችሉበት ሁኔታ እየተመቻቸ ይገኛል።

የእምነበረድ ማዕድን በክልሉ በሦስት ዞኖች ይገኛል የሚሉት ኃላፊው፤ ማዕድኑ በአብዛኛው በመተከል ዞን አካባቢ እንደሚገኝ አስታውቀዋል። በዞኑ ማዕድኑን የማልማት ሥራ እየተካሄደ መሆኑን ጠቅሰው፣ በአሶሳ እና በከማሼ ዞንም እምነበረድ እንደሚመረት ይገልጻሉ።

ኃላፊው እንዳሉት፤ በክልሉ ስላለው የእምነበረድ ድንጋይ ክምችት ጥናት እየተደረገ ነው። በጥናት የተረጋገጠ ነገር ባይኖርም በሄክታር በርካታ መጠን ያለው ክምችት እንዳለ መረጃዎች ያሳያሉ። እስካሁን ባለው መረጃ ለማንኛውም በዘርፉ ለመሰማራት ለሚፈልግ ባለሀብት የሚበቃ ክምችት በክልሉ አለ።

ቀደም ሲል የክልሉ የእምነበረድ ምርት በብሎክ ብቻ እየተመረተ ወደተለያዩ ቀለሞችና ቅርጻ ቅርጾች የሚቀይሩ ፋብሪካዎች እንደሚወሰድ የጠቆሙት ኃላፊው፤ አሁን ላይ በክልሉ የተቋቋመው ፋብሪካ ብሎክ የማምረት ሥራ ከጀመረ ወዲህ የተሻለ ምርት ማምረት እየተቻለ መሆኑንም ይናገራሉ። ፋብሪካው በሚፈለገው መጠንና ቅርጽ ብሎክ በመቅረጽ እምነበረድ እያመረተ መሆኑን ጠቅሰው፣ የተለያዩ ነገሮች ለማምረት የሚያገለግለውን ተረፈ ምርት መልሶ መጠቀም ላይ ግን ክፍተቶች እንዳሉበት አመላክተዋል።

የእምነበረድ ተረፈ ምርት የተለያዩ ነገሮች ሊመረትበት እንደሚችል ኃላፊው ጠቅሰው፣ ለአብነት በጥቃቅንና አነስተኛ የሚደረጁ ወጣቶች ከተረፈ ምርቱ የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችን፣ የቀለም ዓይነቶችን እና የመሳሰሉትን ሥራዎች መሥራት የሚችሉበት ፋብሪካ እንደሚያስፈልግ ይጠቁማሉ።

አሁን ላይ ያለው ፋብሪካ የብሎክ ሥራውን ብቻ እንደሚሰራ አመልክተው፣ በቀጣይ ከዚህ ጎን ለጎን የቀለም ፋብሪካ ቢቋቋም ያለውን አቅም አሟጦ በመጠቀም ውጤታማ ሥራ መሥራት ይቻላል ይላሉ። ከተረፈ ምርቱ ብዙ ነገሮች ማምረት እየተቻለ ብዙ ተረፈ ምርት እየባከነ መሆኑን ተናግረው፣ ይህ ለብዙ ሥራ ሊውል የሚችል ተረፈ ምርት እንደማንኛውም ዓይነት ቆሻሻ እየተጣለ እንደሆነ ይናገራሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ እስካሁን ባለው መረጃ ከተረፈ ምርቱ ቀለም ማምረት ይቻላል፤ መድኃኒቶችንም እንዲሁ ማምረት ይቻላል፤ በቀጣይ በተረፈ ምርቱ ላይ ትኩረት ተሰጥቶት ይሰራበታል።

በክልሉ በተመሳሳይ እምነበረድን ለማምረት የሚችል ሌላ ሁለተኛ ፋብሪካ በግንባታ ሂደት ላይ እንደሚገኝ አቶ ካሚል ጠቅሰው፣ «ግንባታው ሲጠናቀቅ እምነበረድ የማምረቱ ሥራ በይበልጥ ይጠናከራል፤ የተሻለ ምርት ማግኘትም ይቻላል» ብለዋል።

ለእምነበረድ ምርት ቀደም ሲል የገበያ ትስስሮች መፈጠራቸውን አስታውሰው፣ ለምርቱ ምንም ዓይነት የገበያ ችግር እንደሌለም አስታውቀዋል። በሥራ ላይ ያለው የእምነበረድ ፋብሪካን የገበያ ሁኔታ ለአብነት ጠቅሰው ኃላፊው ሲያብራሩም፣ እስካሁን ምንም ዓይነት የገበያ እጦት አጋጥሞት እንደማያውቅ አመልክተዋል። እንዲያው ፋብሪካው ቅድመ ክፍያ ተከፍሎት እንደሚያመርት ነው የተናገሩት።

ፋብሪካው እምነበረድ በራሱ ቦታ ላይ እንደሚያመርት ጠቅሰው፣ ገበያ ለማፈላለግ ሲል የሚያጠፋው ጊዜ እንደሌለና የማምረት ኃላፊነቱን ብቻ እንደሚወጣ አስታውቀዋል። ፋብሪካው እምነበረድ በማምረት ሥራ ዋንኛው ትኩረት መሆን ያለበት ማምረት መቻል ብቻ መሆኑን ጠቅሰው፣ የገበያ ችግር የለበትም ሲሉ ተናግረዋል።

ሌሎች አምራቾችም አዲስ አበባ አካባቢ ካሉ ፋብሪካዎች ጋር ውል ገብተው እንደሚሰሩ ጠቅሰው፣ አንዳንድ አምራቾች ደግሞ ሌላ ቦታ ላይ ፋብሪካ እንዳላቸውና ምርታቸውን ወስደው ቀጣዩን ሥራ እንደሚሰሩ ኃላፊው ጠቁመዋል።

አሁን በዘርፉ የተሰማሩ አብዛኛዎቹ አምራቾች የካምፕ እድሳት በማድረግ ወደ ማምረት ሥራ ለመግባት የሚያስፈልጓቸውን ቅድመ ዝግጅቶች እያደረጉ መሆናቸውን የሚናገሩት ኃላፊው፤ ይህ ደግሞ ዘንድሮ ምርቱ በተሻለ ሁኔታ እንደሚመረት እንደሚያመለክት ተናግረዋል። ከዚህ በፊት ባለው የክልሉ ጸጥታ ሁኔታ ካምፓቸውን ሳያድሱ የቆዩ ሌሎች አምራቾችም እንዲሁ ዘንድሮ ካምፓቸውን አድሰው ወደ ሥራ እየገቡ መሆናቸውን ጠቁመዋል። ይህ ሁሉ ሲሆን ማዕድኑ በተሻለ ሁኔታ ይመረታል፤ የተያዘው እቅድም ከግብ ይደርሳል ብለዋል።

በክልሉ አሁን ያለው ሁኔታ የእምነበረድ ምርት መሻሻሎች የታየበት መሆኑን ጠቅሰው፣ ሁሉም አምራቾች ወደ ማምረት ሥራው ሲገቡ የተሻለ ምርት እንደሚገኝ ጠቁመዋል። ይህን ለማስቀጠል ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉም አረጋግጠዋል።

በክልሉ የሥራ እድል በመፍጠር ረገድ የታየውን አፈጻጸም በተመለከተ ሲያብራሩም በ2016 በጀት ዓመት በማዕድን ዘርፍ ለአንድ ሺ453 ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር መታቀዱን ገልጸዋል። በሩብ ዓመቱም 1ሺ 159 ያህል ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር ተችሏል ብለዋል። ይህም ከአፈጻጸም አንጻር ሲታይ የተሻለ የሥራ እድል የተፈጠረበት መሆኑን አመልክተው፣ የሥራ እድሉ በአብዛኛው በወርቅ ማዕድን ዘርፍ የተፈጠረ መሆኑን ተናግረዋል። በእምነበረድ ፣ በድንጋይ ከሰል እና በሌሎች ማዕድናት ላይ ያለው የሥራ እድል ፈጠራ ብዙ የሚባል እንዳልሆነም ገልጸዋል።

የሀገሪቱ የግንባታ ዘርፍ እንደ እምነበረድ ያሉ የግንባታ ማጠናቀቂያ ምርቶች በስፋት እንደሚያስፈልጋት ይታወቃል። በአሁኑ ወቅት አብዛኛው የግንባታ ማጠናቀቂያ ከውጭ እንደሚገባም መረጃዎች ያመለክታሉ። ለእዚህም ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሬ እየወጣ ነው። በሀገር ውስጥ ሊመረቱ የሚችሉ የግንባታ ማጠናቀቂያዎች ጭምር ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ እየተደረገ ነው። የዚህ አንዱ ምክንያት ደግሞ በሀገሪቱ የግንባታ ማጠናቀቂያ ምርቶች ላይ ያለው የአመለካከት ችግር መሆኑ ይጠቆማል።

በሀገር ውስጥ ከሚመረቱ የግንባታ ማጠናቀቂያ ምርቶች አንዳንዶቹ የጥራት ችግር እንደሚስተዋልባቸው ቢታወቅም፣ በጥራታቸው ጥርጣሬ ውስጥ የማይገቡም እንዳሉም አቶ ካሚል የክልሉ የእምነበረድ ምርት ምንም ዓይነት የገበያ ችግር የለበትም ሲሉ ከሰጡት መረጃ መረዳት ይቻላል። ይህን ምርት በስፋት እንዲመረት በማድረግ በግንባታ ማጠናቀቂያ ግብዓቶች በኩል ያለውን ክፍተት በተወሰነ መልኩ ለመሙላት ይቻላል። ይህ መሆኑ ሀገሪቱ የግንባታ ማጠናቀቂያ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በስፋት በማምረትና በመጠቀም ከውጭ የሚመጡ ተመሳሳይ ምርቶችን ለመቀነስ እያከናወነች ላለችው ተግባር ፋይዳው ከፍተኛ ነው።

የእምነበረድ ማዕድን በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በስፋት ይገኛል። ይህም ማዕድን በስፋት ለማልማት የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የግንባታውን ዘርፍ የግንባታ ማጠናቀቂያ ችግር ለመፍታት የሚደረገውን ጥረት ማገዝ ይገባል። ለእዚህም ሰላምን በማረጋገጥ በኩል እየተከናወኑ ያሉ ተግባሮችን አጠናክሮ ከመቀጠል በተጨማሪ ለዘርፉ ኢንቨስትመንት ትኩረት ሰጥቶ መስራትም ያስፈልጋል።

## መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

# የሕይወት ሰሌዳ

**በትረ ሙሴ (መልከ ጼትዮጵ)**

እንደ ልጅነቴ እግዜር ቢወደኝ እላለሁ። በልጅነቴ ውስጥ እግዜር የሌለበት አልነበረም። አይደለም ለምኜውና ደጅ ጸንቼው እንዲሁ ያማረኝንና ያሰኘኝን ካላንዳች ልፋት ነበር የሚሰጠኝ። ሌላው ቀርቶ የሆነ ወዳጄ ላይ ያየሁትንና ያማረኝን ልብስ ቤት ግዙልኝ ብዬ ሳላለቅስ ነበር ቅዳሜ ወይም ረቡዕ በአንዱ የገበያ ቀን አባቴ ሸምቶ የሚያመጣልኝ። ፍላጎቴን በአባቴ ፍላጎት ውስጥ አስቀምጦ ያዘባንነኝ ነበር... አይ እግዜር።

በልጅነቴ ጥብቆዬ ላይ በተፈጠረች ትንሽዬ ቀዳዳ ገላዬ ይታይ ነበር። ያልተቀደደ ሱሪና ጥብቆ የለኝም። እንዴት እንደሚቀደድ ሳላውቀው ከኋላ በኩል ሱሪዬ ሳስቶ ቀዝቃዛ ንፋስ ሲጀልጠኝ ነው የማውቀው። የሰፈራችን አስቀያሚው ልጅ እኔ ነኝ። በፉንጋነት የሚበልጠኝ አንድ ጓደኛ የለኝም። በሰፈር ጓደኞቼ የወጣልኝ ‹ዲያቢሎስ› የሚል ቅጽል ስም አለኝ። ይሄን ስም አባቴ ፊት ደፍሮ የሚጠራ አንድ ጓደኛ የለኝም። ለአባቴ የነፍሱ ጌጥ ነኝ። በአባቴ በኩል ከጓደኞቼ ሌላ ነኝ። ጓደኞቼን የምበልጣቸው የአባቴ ጥላ ሲያርፍብኝ ነው። ሁሌ እሁድ እሁድ ሰፈራችን ካለ ሆቴል ይወስደኝና ኬክና አይስክሬም ይገዛልኛል። እንዲህ ዓይነቱን ነገር እኔ ካልሆንኩ የትኛውም ጓደኛዬ በአባቱ በኩል አድርጎት አያውቅም። አባቴ በሄድኩበት ሁሉ ከጓደኞቼ ተንኮል የሚሰውረኝን እግዜርን ይመስለኛል። እንዲህ ካልሆነ ምን ሊሆን ይችላል?

ጓደኞቼ በእኔ ተፈጥሮ ነው የሚዝናኑት። ነፍስ የሌለው ወይም ደግሞ የማያመኝ እየመሰላቸው ለየትኛውም ክፉ ነገር እኔን ነው የሚመርጡት። ለምንም ነገር መሞከሪያቸው ነኝ። የፈሩትንና የሰጉትን ነገር በእኔ በኩል ነው የሚደፍሩት። አንድ ጊዜ ደፈቃ እንለማመድ ብለው ሁሉም ጓደኞቼ በየተራ አንገታቸውን ውሃ ውስጥ ከተቱ። እኔ እበልጣለሁ... እኔ እበልጣለሁ ከሚል ክርክር በኋላ የእኔ ተራ ደርሶ በል አንተ ደሞ ጀምር አሉኝ። ስፈራ ስቸር ወደ ውሃው ገባሁ። እንዳልወጣ ጭንቅላቴን ይዘው ተባብረው ደፈቁኝ። ሳንባዬ አየር ሲያልቅበት ሁለመናዬ በአየር ናፍቆት ደበነ። መንፈራገጥ ሳቆም፣ አቅም አጥቼ እጃቸው ላይ ስዝለፈለፍ፣ ስሞት ለቀቁኝ። ግን እግዜር እንደ አላዛር በሙት ነፍሴ ላይ ሕይወት ዘርቶ ቀሰቀሰኝ። በዛ በድንነቴ ውስጥ ለማንም ያልተሰማ... ‹ነጋ..አንተ ነጋ ተነስ? የሚል ድምጽ ስሰማ ነበር። ከዛ ድምጽ በኋላ ነው የነቃሁት። የዛ ቀን የደፈቃ ቆይታዬ ማንም ያልቻለው የምንጊዜም ሪከርድ ሆኖ ተቀመጠልኝ። እግዜር ሁሌ ሪከርዴ ነው። በጣም የሚገርመው ደግሞ ጓደኞቼ በምንም ችለውኝ አያውቁም። በግድና በውድ ፈቅጄም ይሁን ተገድጄ በተወዳደርኩባቸው የልጅነት ጨዋታዎች ውስጥ ፊተኛ ነበርኩ።

በሕይወቴ ያልተመለሱልኝ ዛሬም ድረስ የሚያመራምሩኝ ሁለት ነገሮች አሉ። አንዱ የሊዲያ ውበት ነው። ሌላኛው ደግሞ ሊዱ ከስንት ሸበላ እና ባለጸጋ ወንድ መሀል እኔን መምረጧ ነው። ትዝ ይለኛል... የሊዱ ውበት... አበባዎች ቀንተው ሲገላምጧት። ጤዛዎች አፍረው ሲያጎነብሱ። ትዝ ይለኛል ሳቋ... ብዙ ወንዶችን ሲያደናብር፣ ብዙ ትዳሮችን ሲያፈርስ። ትዝ ይለኛል አይኗ... በአንድ ጊዜ ጥቅሻ እኔ ነኝ ያለን ወንድ አፍር ከድሜ ሲያስግጡ። እንደጨረር ሲዋጉ... እንደ ጦስ ዶሮ ሲያንደፋድፉ። ትዝ ይለኛል አፍንጫዋ..ወጭ ወራጁን ሲያደናብር። አልፎ ሂያጁን ሲያስቀላውጥ። በውበት ሰገነት ላይ ሲንጎማለል። ትዝ ይለኛል ከናፍርቷ... የዘመን ጌጥ አልቦ ሆኖ ከፊት ለፊት ጸዳሏ ላይ ተሰይሞ። የነፍስ ብርድ... የልብ ወበቅ ይሄን ሆኖ ላያት ሁሉ እዳ ሲሆን። ትዝ ይለኛል አረማመዷ... ትዝ ይለኛል እግር አጣጣሏ። የመላዕክት በሚመስል ዝማሜ ስትዘም። ሥርዓት በዋጀው ቄንጠኛ ርምጃ ስታገድም። ትዝ ይለኛል ሰውነቷ... ትዝ ይለኛል አካል ምስሏ..በውብ ጥበብ እንዳጌጠ የሸራ ላይ እንጥፍጣፊ ግርማ ለብሶ... ጸዳል ወርሶት። ትምህርት ቤታችን ውስጥ ውድና ንጹህ ልብስ ከሚለብሱ አስር ዘመነኛ ሴቶች ውስጥ አንዷ ናት። ትዝ ይለኛል... የጸጉሯ ርዝመት... የሰውነቷ ቅላት። ትዝ ይለኛል... ቆመው የሚያዩዋትን ወንዶች አልፋ ወደእኔ ስትመጣ። ከክላስ ስትወጣና ስትገባ እንደቦርሳዋ ጎኗ ለጥፋኝ እዩን ስትል።

በሊዱ በኩል ልጅነታችን ተመለሰ። በልጅነታችን አንድ ዓይነቶች ነበርን። ስናጠፋ፣ ስንደሰት፣ ስንዋሽ፣ ስንሰርቅ አብረን ነበር። በአንዲት ሴት ነፍስ ላይ ዳግም ለመለምን። ፍቅር ትዝታ ያጠፋል፣ ወዳጅነትን ያስረሳል ሲባል የምሰማው ወሬ በእኔና በጓደኞቼ ላይ ሰርቶ እውነት ሆኖ አገኘሁት። በሊዱ በኩል አብዛኞቹ ጓደኞቼ ኩርፍ ናቸው። በእሷ በኩል ፍቅር መልኩን ጥሏል። ምንም ከሌለኝ ከእኔ በቀር ሁሉም ጓደኞቼ በእሷ ፊት አሪፍ ሆኖ ለመታየት የብኩርና ውድድር ይዘዋል። እኔ ድህነቴንና ፉንጋነቴን አምኜ ለውድድር አልቀረብኩም። ምን ባምር ነፍሷን እንደማልማርካት ስላወኩ አርፌ ቁጭ ብያለሁ። ወደእኔ እንደማትመጣ እያወኩ ግን አፈቅራት ነበር። በታሪክ በብዙ ወንዶች የተፈቀረች የመጀመሪያዋ ሴት ትመስለኛለች። ክፍላችን ውስጥ 60 ተማሪ አለ። ከስልሳው 28ቱ ወንዶች ነን። በ28ቱም ተፈቅራለች። ፍቅራቸውን ከደበቁና ከሚያስመስሉ አንዳንድ ተማሪዎች በቀር በሁሉም ተጠይቃለች። ሊዱ እንደ ክሊዮፓትራ የጓደኞቼን አስተሳሰብ እንዳለ ነው የቀየረችው። በክሊዮፓትራ አፍንጫ የዓለም ካርታ እንደተቀየረ የጓደኞቼም አስተሳሰብ፣ ሥነ ልቦና ተቀይሮ ነበር። ለእሷ ያልገጠመ፣ ስለእሷ ያላዜመ አንደበት የለም። በሊዱ ውበት በኩል ብዙ የተደበቁ ተሰጥኦዎች አደባባይ ወጥተዋል። ከተንኮልና ከውሸት ውጭ ተሰጥኦውን የማያውቀው ፉንታ እንኳን በእሷ በኩል ነው ምርጥ ገጣሚ የወጣው።

እኔ ከምኑም ውስጥ የለሁበትም። ፍቅሬን በልቤ ይዤ ዝም ጭጭ። በዛ መልኬ ባወራት ነበር የሚገርመው። ወዳጆቼ የጣሉብኝ የትንሽነት መንፈስ እንዲህ ባለው ሁኔታ ውስጥ ነው ነፍስ የሚዘራው። ዲያቢሎስ እየተባልኩ አድጌ፣ በመልኬ የወዳጆቼ መሳቂያ ሆኜ ኖሬ እሷን ለመቅረብ አቅም አጣሁ።

የሆነ ነገር ትውስ አለኝ። ጉዳዬን ለፈጣሪ ስሰጥ እንዲህ ነኝ። ከረሳሁት የሆነ ጠቃሚ ነገር ጋር ተገናኘሁ። የሆነ ጊዜ ላይ ምን አሰኝቶት እንደሆነ እንጃ እናቴን እንዴት እንዳገባት ነግሮኝ ነበር። ያ የአባቴ ንግግር መጣብኝ። ‹እናትህ በጣም ቆንጆ ሴት ነበረች። እኔ ደግሞ እንደምታየኝ አልቅት ነኝ። ከውበቷ የማይወዳደር መልኬን፣ ከሴትነቷ የማይቆም ወንድነቴን ያስጠጋሁት በዝምታ ነው... ሁሉም ስለእሷ ሲጮሁ ዝም በማለት› አለኝ። በእጁ የያዘውን ጉርሻ ወደአፉ እያለ ‹የምትፈልገውን ነገር የአንተ ለማድረግ ከሌሎች ጋር አትዋደቅ... አትፎካከር ዳር ሆነህ ተመልከት። እናትህን የእኔ ያደረኳት ከሚፎካከሩላት እልፍ ወንዶች ውስጥ ሳልደባለቅ ዳር ቆሜ በማየት ነው› አለኝ አላምጦ የጨረሰውን ምግብ ወደሆዱ እየሰደደ።

ንግግሩን ሲቋጭ በአንዲት መቼም በማትረሳ ወርቃማ ንግግር ነበር ‹ፍቅር ከጩኸት ይልቅ ዝምታ ውስጥ ነው ያለው። ዝም ካላልክ በጩኸት ፍቅርን አትደርስበትም። በመተው ውስጥ ብዙ መፈላለግ አለ። የምትወዳትን ሴት የረሳሃት ምሰል። በጥበብ ውስጥ ዝም ካልክ በሞኝነት ከሚጮሁ እልፍ ነፍሶች በላይ የአንዲትን ሴት ነፍስ መማረክ ትችላለህ› አለኝ። በተለይ የመጨረሻዋ ንግግሩ ስሰማ በአባቴ አፍ እግዜር የተናገረ ነበር የመሰለኝ።

የእናቴንና የአባቴን ታሪክ በሊዱ ላይ ልተገብረው ሀ አልኩ። በአባቴ ምክር ሄጄ... ሊዱን የውሸት ረሳኋት። በብዙ ወንዶች ከበባ ውስጥ ያለችውን ነፍሷን የዘነጋኋት መሰልኩ። ሊዱ የእኔ ትሆናለች ብዬ አይደለም በውኔ በህልሜም አልገመትኩ። ለዛ ፊትና ለዛ ወንድነት ሚስት ትሆናለች የሚል አንድም ጥርጣሬ በአእምሮዬ ውስጥ አልነበረም። የሆነው ሆነና... ሊዱ የኔ ሆነች። ዝምታዬ ፈጠራት። በነዛ ሁሉ በሚጮሁ አፎች ላይ ተረማምዳ ዝም ወዳልኩት ወደ እኔ መጣች። በሊዱ ጉዳይ እግዜር ቀድሞ አባቴ ይከተላል። ለዛች ነፍስ ከዝምታ ሌላ አስተዋጽኦ አልነበረኝም። ከልጅነቴ ጀምሮ ላልተወኝ ጌታ እኩል ባይሆን የማያሳፍር ውለታ ባስብ አጣሁ።

የአባቴ ንግግር መነሻውና መድረሻው አሁን ነው የገባኝ። ማንም እንደማያገባኝ ስላወቀ፣ የትኛዋም ሴት እንደማትቀርበኝ ስለገባው ይመስለኛል እንደዛ ያለኝ። በእማዬ ማህጸን በእኔ በኩል ራሱን ደግሟል። በሊዱ ማህጸን እኔን እንዳልደግመው ለፈጣሪ ሌላ አደራ አለኝ። በአንድ ቤት ውስጥ እኔና አባዬ በቂዎች ነን። ልጄ እንደ እኔ ለምንም ነገር እግዜርን የሚያስቀድም ሆኖ እንዲኖር አልፈልግም በአንዳንድ ነገሮች ላይ ራሱን እንዲያጋፍጥ... ራሷን እንድታጋፍጥ ከእኔ መልክ የራቀ ሰውነት እሻለሁ። እግዜር ባይቀድምለት ኖሮ ይሄ ፊት ከዛ እዚህ ለዛውም ሊዱ ላይ በምን ኃይሉ ይወድቅ ነበር? አይረባም በተባለው ልጅነቴ ውስጥ ብዙ መርባቶችን አኑሮ፣ በሊዱ ደጅ ላይ ሲያቆመኝ እግዜርን ከልቤ ሻትኩት። ለሆነልኝ የምሆንለት ባይኖርም፣ ላደረገልኝ የማደርግለት በጣም እንዲሁ ግን አፈቅረዋለሁ። ነፍሴ በእሱ ጫንቃ ላይ እሽኮኮ ላይ ባታርፍ ምን ይውጣት ነበር?

# ዓለም አቀፍ

## 10 ሺዎችን በጀልባ ወደ እንግሊዝ ያስገባው

## ሕገ-ወጥ ሰው አዘዋዋሪ ተፈረደበት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በእንግሊዝ ቻናል በኩል ሰዎችን በሕገ-ወጥ መንገድ በማሻገር ከተሳተፉት የአዘዋዋሪ ቡድኖች አንዱን ሲመራ የነበረው ግለሰብ በቤልጂየም የ 11 ዓመት እስራት ተፈረደበት።

ትናንሽ ጀልባዎችን በመጠቀም 10 ሺህ ሰዎችን ወደ ዩናይትድ ኪንግደም እንዲገቡ ካደረጉት መካከል ቀንደኛው የ30 ዓመቱ ሄዋ ራሂምፑር እንደነበር ፖሊስ ያምናል።

ራሂምፑር እ.አ.አ በ2016 ብሪታንያ ሲደርስ እና ጥገኝነት ሲጠይቅ 23 ዓመቱ ነበር። በወቅቱም ኢራናዊ ኩርድ በመሆኑ ወደ ሀገሩ ቢመለስ ችግር እንደሚያጋጥመው ተናግሯል። በአውሮፓውያኑ 2020 እንዲቆይ ፈቃድ ተሰጠው።

በዩናይትድ ኪንግደም የመቆየት ፍቃድ የተሰጠው ራሂምፑር ከጓደኛዋ ጋር በለንደን ፀጉር ቤት ከፈተ። ቀጥሎም ብሪታንያን ለሚመራው ትልቅ የወንጀል ኦፕሬሽን ማዕከል አደረጋት።

ለስደተኞች መሻገሪያ የሚያገለግሉ ጀልባዎችን፣ ሞተሮችን እና የሕይወት አድን ጃኬቶችን የሚያቀርቡ ቡድኖች አለቃ ሆነ። እቃዎቹን ከቱርክ እና ከቻይና በመግዛትም ወደ ጀርመን፣ ቤልጂየም እና ኔዘርላንድስ አጓጉዟል።

ጀልባዎቹ ወደ ሰሜናዊ ፈረንሳይ የባህር ዳርቻ አቅንተው በካሌ እና ዱንኪርክ ለሚገኙ ስደተኞች ተሰጡ። ሴቶች እና ሕጻናትን ያካተቱት ስደተኞች በጀልባዎቹን ተጠቅመው እንዴት ወደ ብሪታንያ መግባት እንደሚችሉ መሠረታዊ መረጃ እየተሰጣቸው ቻናሉን አቋርጠዋል።

አንዳንዶቹ ጀልባዎች ደህንነታቸው ያልጠበቁ፤ በፕላስተር እና በእንጨት ጭምር የተያያዙ እንደነበር ተነግሯል።

የስደተኞች ጉዳይ ባለሙያው ስቴፍ ያንሰንስ ለቢቢሲ እንደተናገሩት በእያንዳንዱ ጀልባ ከ30 እስከ 40 የሚደርሱ ሰዎች እንዲጫኑ ተደርጓል። “አሻጋሪዎቹ ለሰው ሕይወት ምንም ክብር አያሳዩም። የሚገርመው ከዚህ በላይ ሞት አለመመመዝገቡ ነው” ብለዋል።

ከ12 እስከ 18 ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ ወደ ዩናይትድ ኪንግደም ለመሻገር ከሞከሩ ስደተኞች 10 በመቶ ለሚጠጉት የራሂምፑር ቡድን ተጠያቂ እንደሆነ ይታመናል።

"ትንንሽ ጀልባዎችን በመጠቀም ሰዎችን የሚያዘዋውር ቡድን መሪ የሆነ ሰው ተጠያቂ ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ነው" ያሉት ያንሰን፤ የፍርዱ ዓለም አቀፍ የሰዎች አዘዋዋሪዎችን ለመዋጋት ወሳኝ ርምጃ እንደሆነ ገልጸዋል። "ጉዳዩ በሰሜን ባህር ከሞቱት 31 ሰዎች ጋር በቀጥታ ሊገናኝ ይችላል" ሲሉም አክለዋል።

ቻናሉን የሚያቋርጡ ሰዎች ሊሞቱ መሆኑን በመግለጽ ራሂምፑር ለፖሊስ እንዲደውል የተነጋገሩበትን የዋትስአፕ መልዕክት ልውውጥ እንዳዩ ያንሰን ገልጸዋል።

በሌላ መልዕክት ራሂምፑር የብሪታንያ ውሃ ክልል እስኪደርሱ እንዲጓዙና በዚያም መጓዝ የዩናይትድ ኪንግደም የባህር ጠረፍ ጥበቃ ቡድን ወደ እንግሊዝ እንደሚወስዳቸው ምላሽ ሰጥቷል። "ከዚህ የመልዕክት ልውውጥ የምንረዳው ትንሽ ገንዘብ ላለማግኘት እነዚህ ሰዎች እስከመጨረሻው እየገፉ እንደሆነ መናገር ይቻላል" ብሏል።

በዩናይትድ ኪንግደም ብሔራዊ የወንጀል ኤጀንሲ እና በቤልጂየም ባለስልጣናት ጥምረት በተደረገ የጋራ ምርመራ፤ እአአ በ2021 በቤልጂየምና ፈረንሳይ ድንበር አቅራቢያ በመኪና ጀርባ ላይ በርካታ ጀልባዎችን አግኝተዋል።

በ2022ም ፖሊስ ራሂምፑርን ምሥራቅ ለንደን ተያዘ። 135 ጀልባዎችን፣ 45 ሞተሮችን እና 1200 የነፍስ አድን ጃኬቶችንም በቁጥጥር ስር አዋለ።

በቁጥጥር ስር የዋለውም በእንግሊዝ፣ በፈረንሳይ፣ በጀርመን፣ በቤልጂየም እና በኔዘርላንድስ ፖሊስ ባደረገው የተቀናጀ ምርመራ ነው። በዓይነቱ ትልቅ በተባለለት የሕግ ማስከበር ዘመቻ በአራት ሀገሮች ውስጥ ከ40 የሚበልጡ ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል።

ራሂምፑር የ80 ሺህ ዩሮ ቅጣትም ተላልፎበታል። ባለሥልጣናት የተወሰነበት የ11 ዓመት እስር ሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎችን ከድርጊታቸው ሊገታ እንደማይችል ያምናሉ። የሰዎች አዘዋዋሪ መረቦች በደንብ የተደራጁ እና ለመለየትም በጣም አስቸጋሪ እየሆኑ ነው።

ራሂምፑር ከታሰረ በኋላም በርካታ ሰዎች በትናንሽ ጀልባዎች ወደ እንግሊዝ መምጣታቸውን ቀጥለዋል። በዚህ የፈረንጆች ዓመት ከ24,200 በላይ ሰዎች ከፈረንሳይ በመነሳት የእንግሊዝን ቻናል አቋርጠዋል። ቻናሉን ለማቋረጥ የሚፈልጉ በርካታ ሰዎችም አሉ።

ስደተኞች በሕገ-ወጥ አዘዋዋሪዎቹ ጀልባ ለመሳፈር ሲሉ ብዙ ገንዘብ ይከፍላሉ። ራሂምፑር የሚመራው ቡድን በ2021 ወደ 52 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ እንዳገኘ ይገመታል።

በጣም አደገኛ የሆኑት አደጋዎች እንኳን ሰዎች በትናንሽ ጀልባዎች ወደ አውሮፓ ለመግባት የሚያደርጉትን ሙከራ እንዲያቋርጡ አላደረጋቸውም። ባለፈው ሰኔ በደቡብ ግሪክ የባህር ዳርቻ ላይ አንድ ጀልባ በመስጠሟ የ500 ሰዎች ሕይወት አልፏል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## ትዊተር (ኤክስ) አዲስ አካውንት ለመክፈት አንድ ዶላር ማስከፈል ጀመረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ኤክስ (የቀድሞው ትዊተር ) አዳዲስ ደንበኞቹን ዓመታዊ ክፍያ ማስከፈል ጀመረ።

የማህበራዊ ትስስር ገጹ በኒውዝላንድ እና ፊሊፒንስ የጀመረው የአንድ ዶላር ዓመታዊ ክፍያ በሌሎች ሀገራትም በቀጣይ ይተገበራል ተብሏል።

ዓመታዊውን ክፍያ የፈጸሙ ሰዎች መረጃዎችን ማጋራት (ትዊት ማድረግ)፣ አስተያየት መስጠት፣ የሌሎች ሰዎችን መረጃ ማጋራት እና ሌሎች አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላሉ። ክፍያውን የማይፈጽሙት ግን መረጃዎችን ከማየት ያለፈ ተሳትፎ አይኖራቸውም ነው ያለው የኤለን መስኩ ኩባንያ ኤክስ።

ውሳኔው ሀሰተኛ አካውንቶች (ስፓም እና ቦት) ለመቀነስ እንደሚያግዝም አስታውቋል።

ባለሙያዎች ግን የኩባንያውን ገቢ ከማሳደግ የዘለለ የሀሰተኛ መረጃ ልውውጥ እና አካውንቶችን በመቀነስ ረገድ የረባ ለውጥ ያመጣል ብለው አያምኑም። ለዚህም ኤክስ በወር በ11 ዶላር በማስከፈል የአካውንት ትክክለኛነት ማረጋገጫ ሰማያዊ ምልክት መስጠት ቢጀምርም ሀሰተኛ አካውንቶች አልቀነሱም የሚለውንም መከራከሪያ አድርገው ያቀርቡታል።

በ44 ቢሊየን ዶላር ትዊተርን የገዙት ኤለን መስክ የኩባንያውን ትርፋማነት ለማሳደግ የተለያዩ አገልግሎቶችን በክፍያ መስጠት ከጀመሩ ወራት እየተቆጠሩ ነው።

የዓለማችን ቀዳሚው ቱጃር ባለፈው ወር ከእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚንን ኔታንያሁ ጋር ባደረጉት ምክክር ሁሉንም የኤክስ ተጠቃሚ ለማስከፈል ማቀዳቸውን መናገራቸው የሚታወስ ነው ሲል አልዓይን ኒውስ ዘግቧል።

# ስፖርት





## ጎተይቶም ገብረሥላሴ በቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን ለአሸናፊነት ትጠበቃለች

ብርሃን ፈይሳ

በሳምንቱ መጨረሻ ከሚካሄዱ የጎዳና ላይ ውድድሮች መካከል አንዱ የቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን ሲሆን፤ ከመላው ዓለም የተሰባሰቡ ድንቅ አትሌቶች በውድድሩ እንደሚሳተፉ ታውቋል። ፈጣን ሰዓት ከሚመዘገብባቸው የግማሽ ማራቶን ውድድሮች አንዱ በሆነው የቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን በሴቶች የዓለም ክብረወሰን የተመዘገበበት ከተማ ነው። በወንዶችም የርቀቱ ሁለተኛው ፈጣን ሰዓት የተመዘገበው በዚሁ ከተማ ነው።

በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ ደረጃ የተሰጠው ይህ ውድድር ዘንድሮ ለ33ኛ ጊዜ ሲካሄድም በርካታ የርቀቱ ከዋክብት እንዲሁም በመም ውድድሮች ስኬታማ የሆኑ አትሌቶች የሚፎካከሩበት ይሆናል። በርካታ ኢትዮጵዊያን አትሌቶች በሚሳተፉበት የዘንድሮው ውድድር በሴቶች አዲስ ክብረወሰን ሊመዘገብ እንደሚችል ተገምቷል። በውድድሩ ከሚካፈሉት መካከል አብዛኛዎቹ ተቀራራቢ የሆነ ብቃት ያላቸው፤ ሶስቱ ደግሞ በርቀቱ ከ1ሰዓት ከ5 ደቂቃ የሆነ ፈጣን ሰዓት ያስመዘገቡ መሆናቸው ክብረወሰን እንዲጠበቅ ያደረገ ምክንያት ነው። እነዚህ የርቀቱ ፈጣን አትሌቶች የሚያደርጉት ፉክክርም ውድድሩን በጉጉት እንዲጠበቅ ከማድረጉ በተጨማሪ አዲስ ነገር እንዲጠበቅ አድርጓል። በርቀቱ የዓለም ክብረወሰን በዚሁ የቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን ሲመዘገብ እአአ በ2021 ኢትዮጵያዊቷ ድንቅ አትሌት ለተሰንበት ግደይ ነበረች ባለድል የሆነችው። ያስመዘገበችው ሰዓትም 1:02:52 ሲሆን ከነገ በስቲያ በሚካሄደው ውድድርም ይህንን ሰዓት ሊያሻሽሉ ይችላሉ ተብለው ከሚጠበቁት አትሌቶች መካከል ኢትዮጵያዊያን በቀዳሚነት ተቀምጠዋል።

የፈጣን ሰዓት ባለቤት ከሆኑና አሸናፊም ይሆናሉ ተብሎ ከሚጠበቁት አትሌቶች አንዷ አትሌት ጎተይቶም ገብረሥላሴ ትገኝበታለች። የኦሪጎን የማራቶን ዓለም ቻምፒዮና እንዲሁም በቡዳፔስት የብር ሜዳሊያ ባለቤት የሆነችው ጎተይቶም፤ በግማሽ ማራቶን 1:05:36 የሆነ ሰዓት አላት። ይህ የግሏ ፈጣን ሰዓት እአአ በ2021 ባህሬን ላይ ያስመዘገበችው ሲሆን፤ ስኬታማ የሆነችበትን ይህንን የውድድር ዓመት በተባበሩት አረብ ኤሜሬትስ በተካሄደ የግማሽ ማራቶን ሁለተኛ ደረጃን ይዛ በማጠናቀቅ መጀመሯ የሚታወስ ነው። ጠንካራዋ አትሌት በአጋጣሚዎችና በሕይወቷ ላይ በደረሱ ከባድ ሀዘኖች ሳትበገር በዓለም ቻምፒዮና መድረክ ውጤታማ መሆኗ ይታወቃል። በማራቶን ስኬታማ ዓመትን ያሳለፈችው ጎተይቶም በዚህ ውድድርም አሸናፊ በመሆን በውድድር ዓመቱ ተጨማሪ ስኬት ለማስመዝገብ ወደ ስፔን ታቀናለች።

ጎተይቶም ውድድሩን አስመልክቶም «65 ደቂቃ የግማሽ ማራቶን ፈጣኑ ሰዓቴ ነው፤ በዚህ ውድድርም 64 ደቂቃ ለመሮጥ ጥረት የማደርግ ይሆናል» ማለቷን የምትሰለጥንበት «ኤሊት ራኒንግ ቲም» በማህበራዊ ድረገጹ አጋርቷል። በመሆኑም በሰከንዶች ብቻ የሚበልጧትን የጀርመንና የኬንያ አትሌቶችን ፉክክር ከሌሎች የሀገሯ ልጆች ጋር በመሆን በርቀቱ ያላትን ሰዓት ታሻሽላለች ተብላ ትጠበቃለች።




አትሌት ጎተይቶም ገብረሥላሴ በቫሌንሺያ ግማሽ ማራቶን ፈጣን ሰዓት እንደምታስመዘግብ ይጠበቃል፤

ሌላኛዋ የርቀቱ ስኬታማ ኢትዮጵያዊት አትሌት ንግስት ሃፍቱ በቫሌንሲያ ከጠንካራ ተፎካካሪዎች መካከል ትጠቀሳለች። አትሌቷ በዓመቱ በኔዘርላንድ እና ጀርመን አሸናፊ ስትሆን ሶስተኛ ተሳትፎዋን በምታደርግበት የቫሌንሲያ ማራቶን አሸናፊ የመሆን እድሏም የሰፋ ነው። ዓመቱን በግማሽ ማራቶን እንዲሁም በሌሎች የጎዳና ሩጫ ያሳለፈችው ያለምጌጥ ያረጋል፣ ከወራት በፊት እዚያው ስፔን ላይ በርቀቱ አሸናፊ የነበረችው ትዕግስት ገዛኸኝ፣ ወጣቷ አትሌት ለምለም ኃይሉ እንዲሁም ፍታው ዘራይ በኢትዮጵያ በኩል በውድድሩ ተሳታፊ መሆናቸውን አረጋግጠዋል።

በወንዶች መካከል በሚካሄደው ውድድር በርካታ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ተሳታፊ ሲሆኑ፤ አብዛኛዎቹ ለቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን አዲስ አለመሆናቸው ለአሸናፊነት እንዲጠበቁ አድርጓቸዋል። በርቀቱ ባለው 58:32 የሆነ ፈጣን ሰዓት ለአሸናፊነት በቅድሚያ ከተቀመጡ አትሌቶች አንዱ አትሌት ዮሚፍ ቀጄልቻ ነው። በቅርቡ በተካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ያልተሳካላት ዮሚፍ በዳይመንድ ሊግ እንዲሁም ለመጀመሪያ ጊዜ በተካሄደው የዓለም የጎዳና ቻምፒዮና ላይ ውጤታማ መሆኑ የሚታወስ ነው። አትሌቱ አምና በቫሌንሲያ በመሮጥ ያስመዘገበው ፈጣን ሰዓት እንደመሆኑ ዘንድሮም ውጤት ያስመዘግባል ተብሎ ይጠበቃል። ሌላኛው ወጣት አትሌት ታደሰ ወርቁም ባለፈው ዓመት በቫሌንሲያ ሁለተኛ ደረጃን ያስመዘገበ ሲሆን፤ ዘንድሮ ለአሸናፊነት ይሮጣል። ከታደሰ በሰከንዶች ብቻ የተቀደመው አትሌት ሀጎስ ገብረሕይወት እንዲሁም የኦሊምፒክ የ10ሺ ሜትር ቻምፒዮናው አትሌት ሰለሞን ባረጋም በውድድሩ ተሳታፊ መሆኑ ተረጋግጧል። ይህም አትሌቶቹ በተደጋጋሚ በብሔራዊ ቡድን እንዲሁም ሌሎች ውድድሮች ላይ አብሮ የመሳተፍ ልምድ ያላቸው በመሆኑ በውድድሩ የሚኖሩትን ተፎካካሪዎች በቀላሉ በመርታት ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ ቅድመ ግምቱን አግኝተዋል።